# ትግላችን

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሄት
በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

---

## አብዮታዊ ትግል

## ከየአቅጣጫው

---

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር ፩

መጋቢት ፲፱፻፸

## ይዘት

ገጽ

— ታጋይ ቢሞት ትግል አይሞትም
በአ/ኢ/ተ/ማ ሥ.አ.ኮሚቴ ....... 1

— በራስ መተማመን ማርክሲዊ ሌኒናዊ መርህ ነው... 5

— ትዝብት ከበይበዳኝ ገረመው ............ 20

— 14ኛ የቦሺዩት ሕብረት የኢ/ተ/ማህበር
የፖለቲካ ውሳኔ ................ 27

— የአንጃኛ ግቡ መቃብር ነው
ከንጋቱ ብርሃኑ ............... 37

———xxxxxx———

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

The Ethiopian Students' Union
in Europe

ኢስጦክሆልም 28|02|78

## ታ ጋ ይ ቢ ሞ ት ት ግ ል አ ይ ሞ ት ም

በየቦታው የሚረግፉ የጓደኞቻችን ደም ያበዘናናል እንጂ ተስፋ አያስቆርጠንም:: ሃዘናችንም ወደቀንከሬ በሚሰውም ወቅሳሰው ትግላችን እየተጠናከረ ይሄዳል እንጂ አይዳከምም:: አድሃሪ ነብሰ ገዳዮች ይህን አላወቁት እንደሆን አቀብያችሁ ለመልከቀት እንነሳቸዋለን:: ዛሬ የኢት ጭቁን ህዝብ ትግል ታጋይ ገሰበቦችን በመግደል ይደመሰሳል የሚለው አስተሳሰብ ከአድሃሪ አእምሮ የሚመነጭ ጎጠረቀት ነበርነት ብቻ ነው::

ታጋይ ገሰበቦችን መግደል ለጊዜው ትግሉን ሊያዳክም የሚችል መሆኑ እርግጥ ነው:: ግን ባፍንጫው በላይ አስረዝሞ ሳበብ ገሰበብ በሙሉ የመጠረጊ ውጤት ትግሉን ማጠናከር ነው:: ስለሆነም ዛሬ የኢትን ታጋዮች በመጠረግ ትግሉን እንቀጭላን የሚል አስተሳሰብ ያላችሁ በሙሉ አድሃሪ ነብሰ ገዳዮች ይህን መራራ ሀቅ መርዶ ፊታችሁ ላይ ለመለጠፍ እንገደዳለን:: ይህን ሀቅ ተቀብላችሁ ገድያችሁን ታማላችሁ ለማለት ሳይሆን የናንተ ነብሰ ገዳይነት የኢት ትግል ከመቀጠት ይልቅ የሚያጠናክረው መሆኑን እንደምናውቅና እንደምናምን በናሳውቃችሁ ብቻ ነው::

የ... ቀበሌ ማህበር መሪ፣ ...አብሲ የአብዮት ቀበቶ ኮሚቴ አባል... በ''ቀጥር ነብስ ገዳዮች'' ተገደሉ:: ወዘተ የሚሉ መራር መርዶዎች በቀን ቢት ወሬት ወዲህ የመንግሥትን ጋዜጣ የሚያጨብቡ በሬ ዜናዎች ሆነዋል:: ይህ ግድያ በግልጽ የሚታዩ በርት ልዩ ጠባዮች ይዟል:: 1ኛ_ ግድያው ምርጥ በሆኑ በትራተኪቢል ሹርቹዎችና ገሰበብ ታጋዮች ላይ ያተኮረል፣ 2ኛ_ የሚበሉት ነብሰ ገዳዮች አይያዙም፣ 3ኛ ባለፈው ከረምት መግቢያ ወዲህ ጀምሮ ጥቀ እያጠ መጥቷል::

የዚህ ግድያ ጠባዮች እንደሚጠቁሙት ሁኔታው ቀጥ ባጠ መንገድ እየጋለበ መምጣት የጀመረው አብዮታችን ወደ ተከላካይነት ባፈገፈገ ጊዜ ጀምሮ መሆኑን ነው:: በመሆኑም ቀኙን ይዋቁር የነበረው ምድረ አድሃሪ በሙሉ ያለ የሌለ ሙንቿውን አብዮቱ በፈጠራቸው የህዝብ ድርጅቶችና ብላን በሆኑ ታጋይ ገሰበቦች ላይ መፈተሽ ጀመረ:: በቀበሌ ማህበራት በመኢሶኔ፣ በገበሬ ማህበራት ላይና ታጋዮች ላይ አተኩረ:: ይህ ጥቃት አጋጣሚ ሳይሆን በተመጠነ አስተያየት የመነጨ ነው:: እነኚህ ነፃ ድርጅቶችና ታጋዮች አበዛሬም ለተገኙት ድሎች ሆኑ ለወደፊትም ለሚገኙት ድሎች አስተማማኝ በመሆናቸው የግድ እነሱን በማጥፋት ተገበር ላይ

መበግሬትን ወረው፡፡ በመደረጃታቸውና በዘረፋቸው ኢትዮ ላይ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ ሃይል በመወበጣቸው የሚያደርጉትን ሁሉ ''ሚበጨር''ሆነላቸው፡፡ ''ቅጥር ነብሰ ገዳዮችም'' ፍላጎታቸውን በ''ሚበጨር''አወረት፡፡

ሌላው የነብሰ ገዳይ ወንጀል ደግሞ በገልጽ የኢ ወ አ ደርን በሆኑ ተራማጆች ላይ የሚፈጸመው ነው፡፡ በተበወፉበት እየተያዙ በገልጽ የተረሸኑ ስያሌዎች ናቸው፡፡ አንጋዶ ከበደ መንገሸንና ሌሎችንም ከያሲ ቆራጥ ታጋዮች ያጣነው በዚሁ ሁኔታ ነው፡፡ አሁንም በቅርቡ በታሰበ 30 ጓዶ ተረፈ፣ ጓዲት አቀናፋ፣ ጓዶ ኢሳበ ታደበ፣ ጓዶ ከበደ ደረበ፣ ጓዶ ለማ ፈዳ፣ ጓዶ ሹመስ አሳና፣ ጓዶ ታደበ፣ ጓዶአሰፋ ነመፈ በተበወፉበት በመንግሥት ወታደሮች በተያዙ በኋላ ያለነዳቸ ፍርዶ ተረሸነዋል፡፡

ይህ መቼም የበውን ልጅ አነበተኛ በባከቂ መብት የሚቀሰ ፍጹም ፋሳዊ ፋሺዝነት ነው፡፡ማሉ ተኞች ሆነው አንጋዉን ቢገኙ ለፍርዶ የሚያቀርቡቸውን መብት ማግኘት ነበረባቸው፡፡ ሁሉተኛው ደግሞ ተራማጅነታቸው በምንም የሚያጠራጥር ነሰበቸ መሆናቸው እየታወቀ በመኢሕን አበልነት በጅ መወርወራቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮ መረሸናቸው ፈጹም ሊገበን አልቻለም፡፡ ሶሻሊዝሞ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የሚያሰሁ የሚለው ደርግ ፍጹም አብዮታዊነቱ በተረጋገጠላቸው በመኢሕን አበላት ላይ እንዲህ አይነቱን አርመኛ ፈጸም ሊያደርገው ቀርቶ ሊያስበው አነጋን በልተገበ ነበር፡፡ ወጫም ወረደ ይህ አይነቱ የተደጋገመ አርመኛ የሶሻሊዝ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የሚያጓከም በመሆኑ የኢ ወ አ ደርን በዘህ ከለል ውስጥ ከሚበበሰቡ ሃይሎች ጋራ አንዲት መታየት እንደሚቻል መጨው ጊዜ ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም የኢ ወ አ ደርን ለ''በውር ቅጥር ነብሰ ገዳዮችም'' በተቀ ተኛ ሥት ሁኔታን እየፈጠረላቸው ነው፡፡ ''በውር ቅጥር ነብሰ ገዳዮች''የሚቀበሩቢን መታፈን ሥስት በሜጫ ቀን ታጋዮች፣ እንደማጅራት መቺ አያደቡ በመጠረስ ላይ ናቸው፡፡ ''ሞበሪቢ ብርሃን ነው ብርሃንን የሚፈራ ማጅራት መቺ ነው''እንዳሰው አንዳ ወዘደር ቅጥር ነብሰ ገዳ ዮችም የኢ ወ አ ደርንም የሞቅበሪቢ ቀያፄ አንደዐር ይፈፉታል፡፡ በዚህ ደረጃ የኢ ወ አ ደርን ለተበሉት ''ቅጥር ማጅራት መቺዎች''በሁኔታው ገሩበት ያላቸው ይመስላል፡፡ ተጠያ ቂነትም በማያወላውል ሁኔታ የቀ ተኛ ይሆናል፡፡ በቅርቡ በነኚህ አይነት ማጅራት መቺዎች ህይወታቸውን ከበውት ቆራጥ ታጋዮች ውስጥ አንዱ ጓዶ ገዘው ጀማ ይገኝበታል፡፡ ይህ ጓዶ በአኢተማ ማህበር አንቀበቃ ውስጥ አበከ አመራር ደረጃ ዶረሰ ትልቅ ሚና የተጫወተ በበዚ ዶን ፣ማህበር ሁስጥ ብዙ አበነተጽኦ ያበረከተ ታጋይ ነበር፡፡ በ75 ዓ.ም ወደ አገር



ቤት ከተመለሰም በኋላ በቀበሌ ማህበር ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ከመሰተሩም በላይ በሊቀ መ በርነትም አገልግሏል፡፡ በአህአፓም ቅጥር ነፍሰ ገዳዮች እንዲገደል ብዙ ሙከራም ተደርጎ በታል፡፡ በመጨረሻም በትግል ዓላም ላይ አንዳለ በ''ቅጥር ነፍሰ ገዳዮች''ጥይት ወዶ ቋል፡፡

ጓዶ ተረፈም የነት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማህበር ውስጥ በፕሬዚዳንትነት ያገለገለ ቆራጥ ታጋይ ነበር፡፡ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አውሮፖ ከመጣም በኋላ የደገፈው ነውስ ከበር-ሥሽን በነበረው በሆላንዶ አገር ያደረገው ትግል ምንም ጊዜ የማይረሳ ነው፡፡ አገር ቤትም ከተመለሰ በኋላ በገምበር ቀደምነት ያልተቋጠበ አብዮታዊ አስተዋጽኦ ያበረከተ ሰው ነበር፡፡ በመጨረሻም የፀረ—አብዮት አመጽን ለመደምሰም ሥራውን ጥሎ በህብዐ ትግል ለመሠማራት ወደበሬው ህዝብ ተቀላቀለ፡፡ በህቡዐ ሥራ አንዳለ በመንግሥት ወታደሮች ከተያዘ በኋላ አረመኔ በሆነ መንገዶ ተረሸኗል፡፡

ጓዲት አቀናፍ፣ የጓዶ ተረፈ ባለቤት የነበረች ቆራጥ ታጋይ ነበረች፡፡ በሆላንዶ ከነውስ ከበርቴ ደገፊው ቡዶን ጋራ ያደረገችው ትግል በአውሮፖ ማህበር ውስጥ ትልቅ የትግል ምእራፍ ይይዛል፡፡ በአገር ቤትም ውስጥ የኢህአፖ ድርጅት ከነበረው በቢቶች ''አስተባባሪ'' አብ ሪሪ ኮሚቴ ጋራ ያደረገችው መሪር ትግልና በመቀሳሰው የኢት ሰራ ህዝብ ድርጅትና ነፃቶ እንዲ ቆስ ያደረገችውን ቀረት ለኢት አብዮት ወዳጆች በሙሉ ህያው እንደሆነ ይኖያል፡፡ ጓዲት አቀ ናፍ በመጨረሻም በህቡእ ሥራ ተሰማርታ ከህዝቡ በመቀላቀል ከፍተኛ አብዮታዊ አስተዋጽኦ በማ በርከት ላይ እንዳለች በዚሁ አሰት ከወደቀት በማአታት ጋራ አብራ ተሰናብታናለች፡፡

ጓዶ ኢሳበ ታደበ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ብዙ ትግል ያደረገ ሃቀኛ ታጋይ ነበር፡፡ ወደ እንግሊዝ አገር ለከፍተኛ ትምህርት በሄደበት ጊዜ በብሪታኒያ የኢት ተማሪዎች ማህበር ውስጥ ከፍተኛ ትግል አድርጓል፡፡ ወደአገርም ከተመለሰ በኋላ ከኢት ጭቁኖች ጉን በመሰለፍ በይታከት በቆራጥነት ይታገል የነበረ ወጣት ነበር፡፡ በመጨረሻም የፀረ—አብዮት ቢሬን ለመ ደምሰም በህቡእ ሥራ ተሰማርቶ በሬውን ህዝብ በማገልገል ላይ እንዳለ ከቀፉት በማአታት ጋራ ከንቅን ተነተርጧል፡፡

ጓዶ ከበደ ደረበም እንደዚሁ በእንግሊዝ አገር የተማሪ ነቅናቄ ውስጥ ከፍተኛ ተጋደሎ ያበየ. ወደ አገርም ከተመለሰ በኋላ በሸዋ ክፍለ ሀገር የህዝብ ድርጅት ተጠሪ ሆኖ ለኢት አብዮት ብዙ የሞ ጓዶ ነበር፡፡ በመጨረሻም በህቡእ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የበሬውን ህዝብ በቆራጥነት በማገልገል እንዳለ በመንግሥት ወታደሮች በመረሸኑ የኢት አብዮት በደሙ አቅልቶ አልፏል፡፡

<u>ጓድ ለማ ፊዳ</u> የሸዋ ህዝብ ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ውስጥ በካድሬነት ያገለገለ ቆራጥ ቀይ አብዮታዊ፤

<u>ጓድ ሽመልስ አበና</u> በከፋ ክፍለ ሀገር ህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት በምክትል ሃላፊነት ያገለገለ ቆራጥ ቀይ ታጋይ አብዮታዊ፤

<u>ጓድ ታደሰ</u> በሸዋ ህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ውስጥ በሹፌርነት ያገለገለ ቀይ አብዮታዊ፤

<u>ጓድ አሰፋ ነመራ</u> እንዲሁ ቆራጥና ቀይ አብዮታዊ፤

አራቱም ጓዶች ጓድ ለማ ፊዳ፤ ጓድ ሽመልስ አበና፤ ጓድ ታደሰ፤ ጓድ አሰፋ ነመራ በዚሁ ዕለት ከተቀሩት ጓዶች በህቡዕ ከተሰማሩበት ጋር ተይዘው በግፍ ተረሽነዋል፡፡

በመጨረሻ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ሊገነዘበው የሚገባ አንድ ቁም ነገር ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡ ዛሬ በየቦታው የሚጠረጠሩት ቆራጥና አብዮታውያን አገሪቱ በረጅም ጊዜ ውስጥ ያፈራቻቸው ናቸው፡፡ እነዚህን ታጋዮች ዛሬ እንደተያዘው ጭፍጨፋ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማጥፋት የሚደረገው ጥረት የኢትን አብዮት ለብዙ ጊዜ ወደኋላ መጎተት ማለት ነው፡፡ ነገር በረጅም እርቀት የኢትን አብዮት በእውነተኛ አሸናፊነት ለመውጣት የሚያግደው ሃይል ፈጽሞ ሊኖር አይችልም፡፡

በመኢሶን አባላት ላይ የሚደረገው ክትትል ይቁም!!
የሞቱት ጓዶቻችን አርማ ይዘን እንታገላለን!!
የታሠሩት የህዝብ ወገኖች በአስቸኳይ እንዲፈቱ
ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ!!
ድል የሰፊው ህዝብ ነው!!

THE ETHIOPIAN STUDENT'S UNION
ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ
IN EUROPE



<u>በራስ መተማመን ማርክሲዊ ሌኒናዊ መርህ ነው</u>

ኢትዮጵያን የውስጥና የውጭ ፀረ አብዮተኞች ባንድነት ወጥረው በያዙት ባሁኑ ወቅት ለተፈጠረት ውስብስብ ሁኔታዎችና ችግሮች፤ ባንድ በኩል በሰፊው ሕዝብ ላይ ፅኑ እምነት ባላቸው ለሰፊው ሕዝብ በቆሙ አብዮታውያንና በሌላ በኩል የሰፊውን ሕዝብ አብዮታዊ ትግል በሚፈሩትና በሰፊው ሕዝብ ላይ ጥርጣሬ ያላቸው ደርግና አስመሳይ ተራማጆች የሚያቀርቡት መፍትሔዎች እንደ ሰማይና ምድር የተራራቁ ናቸው፡፡

አብዮታውያን ባሁን ጊዜ ምንም እንኳ በአብዮቱ ላይ ከባድ ፈተና ቢደርስም፤ የኢትዮጵያም ዳንበር ቢደፈርም ዘለቄታ ያለው መፍትሄ የሚገኘው አብዮቱ ገፍቶ ግቡን ሲመታ ብቻ እንደሆነ ያምኑበታል፡፡ ደርግና የቀኝ አድርባዮች በመከተል ላይ ያሉት አቋም ግን አብዮቱን ጭራሽ ለቅልበሳ የሚጋብዝ ሆኗል፡፡ ለተነሱት አያሌ ችግሮች በሰፊው ሕዝብ ላይ እምነት ከመጣል ይልቅ በውጭ እርዳታና በጦር ኃይል በመመካት ለጊዜው የመደብ ትግሉን አቁሞ ጊዜያዊ መፍትሔዎች ካገኙ በኋላ አብዮቱን መቀጠል ይቻላል በማለት ፀረ አብዮታዊ ድርጊቶች በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡

ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ተነስተን የሌሎች አገሮች አብዮት ታሪክ መለስ ብለን በመመርመር የተከሰቱትንና የተጋፈጡትን ምክንያቶች ስናጤነው ለአገራችን አብዮት ዋስትና ራሱ የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ብቻ መሆኑንና ብሎም ሰፊው ሕዝብ ነቅቶ ተደራጅቶና ታጥቆ በራሱ ላይ ተማምኖ ኢምፔሪያሊዝም ፊውዳሊዝም ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ላይ ዘምቶ ካልደመሰሳቸው በስተቀር አብዮቱ ግቡን እንደማይመታና የተነሱትም ችግሮች ዘለቄታ መፍትሔ እንደማይገኝላቸው እንረዳለን፡፡

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የአገሩ ታሪክ ሰሪ የአብዮቱ ባለቤት እንደመሆኑ መጠን አብዮታውያን በራስ መተማመን በሚለው መርህ ሰፊው ሕዝብ በአብዮቱ እንዲሳተፍና ያለውን ሙሉ ኃይል አስተባብሮ የአሮጌውን ስርዓት ተቃውሞ ገርስሶ አዲሱን ስርዓት እንዲገነባ ፍፁም ነፃ የሆነች ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያን እንድትመሠረት ይታገላሉ፡፡

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ትግል የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ትግል አንዱ አካል እንደመሆኑ መጠን ከሶሺያሊስት አገሮችና ከዓለም ተራማጅ ኃይሎች ድጋፍ አገኝቷል፡፡ በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ አብዮታውያን ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

አብዮታችን ከያለበት ውጋና በማግኘቱ ደስ ተስኘተዋል:: የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከሁሉ አስቀድሞ ግን የአብዮቱ ባለቤት በመሆኑ "ዕርዳታ ውጋና እንጂ ወሳኝ አይደለም" በማለት ሰፊው ሕዝብ ይበልጥ ንቃት ድርጅትን ትጥቅን አሟልቶ ያለውን ሙሉ ኃይል አስተባብሮ በመጀመሪያ ደረጃ በራሱ ተማምኖ ጠላቶቹላይ እንዲዘምት ከፍ ያለ ትግል አካሂዷል:: ባገራችን ምንም እንኳ ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች በኖሩም እምነታችን ከሁሉ አስቀድሞ በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብና በኢትዮጵያ ምድር ሃብት ላይ መሆን እንዳለበት ከዚህ ዓይነቱ እምነት መዛነፍ ጭምር ፅሉትና ብሶቶቹን በውጭ ኃይሎች ላይ ብቻ መጣል ያመጣን ዕለት የተካሄደ አብዮትና ብሔራዊ ነፃነታችንንም እንደሚደፈር በየጊዜው አስረድተዋል:: ቅስቀሳም አድርገዋል::

አብዮታዊያን በሰፊው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ላይ እምነት ይኖረንና አብዮታችንን እናካሄድ ቢሉ ለተነሱት ችግሮች ሁሉ ካገሪቱ ሁኔታዎች ተነስተው ባይንባዊ መፍትሔዎች እያቀረቡ ነው:: ለዚህም በሰፊው ሕዝብ አስቀድሞ ኃይሉን ሰብስቦ እንደገና ቅስቀሳና ጠላቶችን እንዲቋቋም ይበልጥ ንቃት ድርጅትን ትጥቅን እንዲያገኝና ከውጭ በምናገኘው ዕርዳታ ላይ ብቻ ተስፋ ሳንጥል ያገሪቱን ክብርና ነፃነት ለጥቂት ጊዜያዊ ጥቅም አንሳንሸጥ አብዮታዊ መስመር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እንድንከተል በመታገል ነው::

1. <u>በራስ መተማመን በመጀመሪያ ደረጃ ሰፊው ሕዝብ ይበልጥ ይንቃ፣ ይደራጅ፣ ይታጠቅ ማለት ነው::</u>

ታሪክ ሰሪው የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ነው ብለን ከተቀበልን ንቃት ድርጅት ትጥቅን አሟልቶ አብዮትን እንዲመራ የሰፊው ሕዝብ ኃላፊነት ብቻ ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ ሰፊው ሕዝብ በመፍጠር ችሎታው ተጠቅሞ ለሚነሱት ችግሮችም ሆኑ ያጋጠሙትን ችግሮች ካገሪ ተጨባጭ ሁኔታዎች ተነስቶ መፍትሔ ማግኘት እንዳለበት ማስረዳትና ለዚህም ቅስቀሳ ማድረግ ያብዮታውያን ግዴታ ነው::

ማንም የውጭ ኃይል የአብዮትን አካሄድ ሊቀይስለት ወይም አብዮትን ሊያራምድለት አይችልም::በአብዮት ታሪክ የለምኗ ታምር ካለም ሰሪው ሰፊው ሕዝብ ኃይሉ በራሱ ላይ ያለው እምነት ብቻ ነው:: በራሱ ላይ እምነት ያለው ሕዝብ ከችግሮቹ እየተማረና መፍትሔ እያገኘላቸው በሚያካሄደው መራራ ትግል እየወደቀም ሆነ እየተነሳ ከዓላማው ዝንፍ ሳይል አብዮትን ያካሄዳል:: እግቡም ይደርሳል::



የኢትዮጵያ ሕዝብ እንቅስቃሴ በገቢራዊ መስክ ቢጀምርም እያሉ ድሎች ተቀዳጅቷል ሆኖም እንቅስቃሴው የሚመራውና የሚያቀናብረው ማርክሳዊ ሌኒናዊ የወዛደር ፓርቲ ባለማግኘቱ ሰፊው ሕዝብ አንዳንድ የመደብ ጠላቶቹን ሲያጠቃ አንዳንድ ደግሞ ሲጠቃና ሲከላከል እዚህ ደርሷል::

የአብዮቱ አመራር ከንዑስ ከበርቴው ደርግ ዕድል ጋር እስከተያያዘ ድረስና ጠቀሜውን የወዛደር ፓርቲ አመራር እስኪያገኝ ድረስ ምንም አስተማማኝ ሁኔታ አይኖረውም:: በመሆኑም ጠቀሜ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በዚህ ረገድ ምን ያህል ከፍ ያለ ተጋድሎ እንደሚጠብቃቸው ለመግለጽ አስቸጋሪ አይሆንም:: በትግሉ ማዕ የተፈተኑ ጠቀሜ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች ከወዛአደሩ መደብ ጋር እስካልተቀላቀሉ ማርክሲዝም ሌኒኒዝምን ሳይበርዙ ሳይከልሱ በሆነ መንገድ የርዕዮተ ዓለም ትግል እስካላካሄዱና ቀራኒያቸውን ፈተው ጠቀሜውን የወዛደር ፓርቲ እስካላመሰረቱ ድረስ አብዮቱ ጠንካራ የሰትና የለውም ማለት ነው::

ሰፊው ሕዝብ ባካሄደው ውጣ ውረድ የተሞላበት ትግል መሰበቱኛውን የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም አገኝቷል::በዚህም ፕሮግራም፣የተጠቀሰው ዓላማ፣ይዘቱ በጊዜያዊ አጣዳፊነት የተቀመጡት ተግባሮች በሥራ መመንዘር ለሰፊሊዝም ለሚደረገው ትግል ዓይነተኛ መሸጋገሪያ ድልድይ ነው::

ሰፊው ሕዝብ በደመና ጠላቶቹ በፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝምና በቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ላይ በማያገም አኳኋን ዱላዎችን እንዲያገኝ ባቀጣኝ ንቃትን ድርጅትን ትጥቅን በጊዜ ጊዜ እያሟላ ትግሉን መቀጠል አለበት:: በዚህ ረገድ ሰፊው ሕዝብ ይበልጥ እንደገና ቅስቀሳና ኃይሉን እንዲሰበሰብ አብዮታዊያን አስሎችን አያሉ ለሰፊው ሕዝብ ሲቆሙ በሌላ በኩል ግን ለፍሰፍስ ንዑስ ከበርቴዎች የሰፊውን ሕዝብ ትግል አብዮታዊ መስመር ሊሜግሩና አብዮትን ለማስቀልበስ እየተፍጨረጨሩ ነው:: በጠቅላላ በሰፊው ሕዝብ ዕምነት ባላቸውና በሌላቸው መሃል የኢትዮጵያ አብዮት አሁን በደረሰበት ደረጃ ቁልጭ ብለው ሁለት መስመሮች ፈልቀዋል::

በሰፊው ህዝብ ላይ እምነት ያላቸው ለሰፊው የቆሙት አብዮታዊያን ባሁን ጊዜ በልዩ ልዩ የአብዮቱ ጥያቄዎች ላይ በሰፊው ሕዝብ ዕምነት ከሌላቸው አስመሳይ ተራማጆች ጋር ከፍ ያለ ርዕዮተ ዓለማዊ ትግል ገጥመዋል::

<u>ጠቀሜው መስመር፣</u> አብዮት የሰፊው ሕዝብ ተግባር መሆኑን የተቀበለና አብዮትም እንዲካሄድ ሰፊው ሕዝብ በረጅም ጊዜ ቅስቀሳና ትግል ነቅቶ ተደራጅቶ ታጥቆ ህዝባዊ አመፅን ሲያካሂድ ብቻ እንደሆነ ያምናል::ስለዚህም ሰፊው

ሕዝብ ቀንደኛ ጠላቶች ላይ የማያዳግም ዱላ እንዲቀዳጁ ፀረ ፊውዳል፣ፀረ ኢም
ፔሪያሊስት፣ፀረ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት የሆኑ ኃይሎችበፈርጃ በፈርጃቸው እን
ዲደራጁ የተራማጆች ህብረተ ወገባርና ወደ ውህደት ተሸጋገሮ ለብ ተማማኙ
ማሌያዊ የወዛደር ፖርቲ እንዲመሰረት በዚህም ፖርቲ አመራር ስር ሕዝባዊ አ
ብዮታዊ ግንባር እንዲቋቋምና ህዝባዊ አብዮታዊ ጦር እንዲገነባ ሰፊው ሕዝብ
የመደብ ጠላቶችን እንዲደመስስ ከፍ ያለ ትግል ያካሄዳል:: ይህን አብዮታዊ
መስመር የሚከተሉ ተራማጆች በአብዮቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ገለጽ የሆነ የ
ታክቲክ አቋማቸውን በመጠቀም ለሰፊውም ሕዝብ በግንባር ቀደምነት ቆመው ይታገ
ላሉ:: ይህ ጠቅና መስመር በአብዮቱ ላይ የተነሱት ችግሮች ከአብዮቱ ጋር
የተያያዙ መሆናቸውን ያምናል::ዱሎችም ለማግኘት አብዮቱን በበለጠ ማፋፋም ነው
ብሎ ቁርጦን ይናገራል:: አብዮቱ አሁን ካለበት ደረጃ ቢያፈገፍግ እንደ
ሚቀለበስ ያስገነዝባል:: ትግሉም ረዥምና መራራ በመሆኑ ሰፊው ሕዝብ በንቃት
በድርጅትና በትጥቅ ብቃ እንዲሆንና በአገሪቱ በሞላ እንዲንቀሳቀስ እንደ እን
ዱ ሰው ሆኖ እንዲነሳ የትግል መሣሪያ የሆነው የዲሞክራሲ መብት ለጭቁኖች
ያለገደብ ለሁሉኑ እንዲለቀቁለት ከሰፊው ሕዝብ ጎን ሆኖ ይታገላል:: የአብ
ዮቱ ወኪሎች የሆኑት የሰፊው ሕዝብ ድርጅቶች እንዲያብቡና በየጊዜው በቢሮክራ
ሲው አሻጥር እንዲደፈራርሱ አድሃሪው ቢሮክራሲው እንዲመታ የተጀመረው ዘመቻ
አብዮታዊ አመራር እንዲኖረው የጠረበበቸም የራሳቸው ዕድል በራሳቸው ለመወሰ
ን ያላቸው መብት ከሥራ ላይ ባስቸኳይ እንዲውል ከፍ ያለ ትግል ያካሄዳል::

በደርግናበአበመባይ ተራማጆች በኩል የሚታየው ግን የተገላቢጦሽ ሆኗል::
እስከተወሰነ ደረጃ ሰፊው ሕዝብ በስተጀርባቸው በነበረ ጊዜ ቆመው የተሰለፉ
መስለው ሰፊው ሕዝብ ትግሉን እያከረረና እያሰፋቸው ሲሄድ የነበራቸውን አብዮ
ታዊ አቋም በመካድ ሰፊው ሕዝብ ከነሱ ውጭ እንዳይነቃ እንዳይደራጅ እንዳይታ
ጠቅ አፍነው ይዘውታል :: በሰፊው ሕዝብ ላይ ዕምነት ማጣታቸው በወላዋይ
የንዑስ ከበርቴ ጠባይ የመጣ መሆኑ ገለፕ ነው:: ሰፊው ሕዝብ እንዳይንቀ
ባቀብ ዲሞክራሲ መብቶችን በፍሬስብርሲኪ በበቦች አፍነው ይዘው ትግሉን ለመገ
ታት ይፍጨረጨራሉ:/የደርግ አባላት ዛሬ ዲሞክራሲ በትግላችን ይሉን ጀምረዋል
ትግላቸው ከማን ጋር ይሆን?/የሲቪልና የሚሊቴሪ ቢሮክራቶች አዋቂ እየተባሉ
ለተነሱት ችግሮች በሚካሄደው ጦርነት እንዲካተፉ ተደርጉ የአገሪቱ ክብርና
ሕልውና ተደፍሯል:: ስአገሪቱም መወረርና ለጭቆን ብሔረሰቦች መጨፍጨፍ ብሮ
ከራሲው ተለቅ ሚና እንደተጫወተ ያደባባይ ምስጢር ሆኗል:: ሰፊው ሕዝብ እን
ደሚፈልገው ለአብዮቱ እንዲዘጋጅ ስለታገ ፤ የፖለቲካው መፍትሔ እንዲዘገይ ተደ
ርጉ ለሚካሄደው ጦርነት በአገደኛ ደረጃ በሰፊው ሕዝብ ተማምኖ የአገራችንን



ድንበር ከማስጠበቅ ይልቅ የውጭ ዕርዳታ እንደ መሠረታዊ ጉዳይ ተደርጉ
ተወስዷል::

እንግዲህ በራስ መተማመን የሚለውን አብዮታዊ መርህ እንከተል በገለ
የአብዮቱ ባለቤት የሆነው ሰፊው ሕዝብ በለሆነ በሱ ላይ ሙሉ ዕምነት ኖሮን
አብዮቱን እንዲያንከባክበውና እንዲጠብቀው እንዲያራምደው ነቃተ ድርጅተ ተጥ
ቅ አሁንም በበለጠ ያሻሉ ነው:: በተለይም የሠፉትን አብዮታዊ ጥያቄዎች
በቀጣኝ መልስ የሚሰጡትን የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገዳች ገደብ ለሁሉኑ
የሚለው የሰፊው ሕዝብ መፈክር በስራ ይተርጐም ነው:: ቢሁኑ ጊዜም አብዮታዊ
ያን መለስተኛው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በሥራ ይመንዘርና ክ
ሰፊው ሕዝብ በይበልጥ እንዲቀሃይ ይላሉ:: ስለሆነም ሰፊው ሕዝብ አብዮቱ ለራሱ
የሚጣለት መሆኑንና ራሱን በራሱ ችሎ የሚያገኘውን ዕርዳታ እንደአጋዥ አድርጉ
ወሰደ የአብዮታዊያን ሰፈር እንደሰበሰበና እንዲጠነክር ለማድረግ እንዲሁም
ቢሮክራሲው እንዲመታ፣ ባቀጣኝ የዲሞክራሲ መብቶችን መለቀቅ አብዮቱ ወሳኝ
ጥያቄ ስላደረገው በዚሁ ረገድ አብዮታዊያን ትግላቸውን አጥፍ ድርብ አድርገው
በመቀጠል ላይ ናቸው::

2. "ዕርዳታ ድጋፍ እንጂ ወሳኝ አይደለም"

የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም ሕዝቦች ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል አንዱ
አካል እንደመሆኑ መጠን ከብዙ አገሮች ድጋፍና እርዳታ አገኝቷል::ይህም የፀረ
ኢምፔሪያሊስቶች ገጼታ ነው::. የኢትዮጵያም ሕዝብ ባገሩ የሚያካሄደው አብዮት
ለዓለም ሕዝቦች የነፃነት ትግል አስተዋጽዖውን ያበረክታል ማለት ነው:: እን
ግዲህ ከሶሻሊስት አገሮችና ከዓለም አቀፍ ዲሞክራሲያዊና ተራማጅ ኃይሎች
ድጋፍ ማግኘት ለምናደርገውም ትግል አስተዋጽኦ ሊያደርግልን በመቻሉ በወዛደር
ዓለም ዓቀፋዊነት መንፈስ የምናገኘው ድጋፍና የምናደርገው ግንኙነት ለአብ
ዮታችን ጠቃሚ እንደመሆኑ ይደገፋል ማለት ነው::

ማህበራችን የኢትዮጵያ አብዮት ዓለም ዓቀፋዊ እርዳታ በማግኘቱ
ደስ የሚለኝ መሆኑንና መደገፉን በየጊዜው ገልጿል:: ኢምፔሪያሊዝም የዓለም ሕ
ዝቦች ጠላት በሆነበት ባሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት አለም አቀፍ ድጋፍ ስለሚ
ያስፈልገው የዓለም ዓቀፋዊ ዕርዳታ ለአብዮቱ ድጋፍ በለሚሆንበአስፈላጊነቱ ማህ
በራችን ያምናል:: ይሁንናም የውጭ እርዳታ ምንጊዜም ቢሆን አጋዥ እንጂ
ወሳኝ እንደማይሆንም የኢትዮጵያ አብዮት በመጀመሪያ ደረጃ መመካት ያለበት
በኢትዮጵያ ሕዝቦች የመታገልና የመፍጠር ችሎታ ላይ መሆን እንደሚገባው በየጊ
ዜው አበረድቷል::

በራስ መተማመን የሚለው አብዮታዊ መርህ የመስመር ጥያቄ እንደሆነ ገለጥ ነው፡፡ ይሁንናም ማህበራችን በዚህ አንፃር ሲደረግ ከሚችሉት ሁለት ስህተቶች አንዱን የጠበቀ ከመቀበቀበ አልቦዘነም፡፡ 1ኛ/ በራስ ላይ መተማመንና ራስን በራስ መቻል የሚለውን መርህ በሁለተኛ ደረጃ፤ የውጭ እርዳታን ደግሞ በአንደኛ ደረጃ መውሰድ የአገርን ነፃነትና ክብር እስከ መሸጥ የሚያደርስ አድኃሪ መስመር መሆኑን፡፡ 2ኛ/ በራስ ላይ መተማመንና ራስን በራስ መቻል የሚለውን በአንደኛ ደረጃ መውሰድና የውጭ እርዳታን አስፈላጊነት ጨርሶ መካድ ደግሞ ግራ ቀደም ስህተት መሆኑን አስረድቶ ሁለቱም መስመሮች ለአብዮታችን አደገኛዎች መሆናቸውን በየጊዜው ገልጧል፤ ለኢትዮጵያም አብዮት ትክክለኛና አብዮታዊ መስመር በመጀመሪያ ደረጃ በራስ ጥረት ወይንም በሰፊው ህዝብ ላይ መተማመንና የውጭ ዕርዳታን እንደድጋፍ ወስዶ /የጉደለ ማሟያ አያደርጉ/ ሁለቱንም እንደ ሁኔታውና እንደጊዜው ማቀነባበር ነው፡፡

በኢ.ሴ.ተማ የ17ኛ ጉባዔያችን ስለ ኢምፔሪያሊዝምና የብሄራዊ ነፃነት ጉዳይ የሚከተለውን አብዮታዊ ውሳኔ አስተላልፏል፡፡ በሰፊው እንጥቀሰው፡፡

“ብሄራዊ ነፃነታችንን ፍፁም ባልሰደፈር ሕዝባችንን በሚያከብር መንገድ ለማስከበር ከሁሉም ይበልጥ በራስ መተማመን የሚለውን መርህ መከተልና በሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡ ማለትም ለአብዮታዊት እናት አገሬ ለመቆት ዘገኝ ስሆነው ሰፊው የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ መመካትና በርሱም እምነት በመጣል የራስ መተማመንን መርህ መከተል ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ መቀስቀስና ለአብዮታዊ ትግልና ስርዓት ማደራጀት ያሻል፡፡ በራስ መተማመንን በሃገራችን ላይ የሚቃጣውን ማናቸውም የኢምፔሪያሊስቶች ተፅዕኖ መክራ የሚያከሽፍ ከመሆኑም በላይ ለአገራችን ክብርና ሕልውና ዘላቂ አስተማማኝ ዋስትና ነው፡፡

ስለሆነም ዛሬ አብዮታችን ተከቦ በተለይ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አስተባባሪነት ከየአቅጣጫው በሚጠቃበት ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም ጭቁን ሕዝቦች አብዮት የማይነጠል አካል መሆኑን ተገንዝበው ሊረዱ የተነሱትን ሶሻሊስት አገሮችና የዓለም ዓቀፍ ዲሞክራሲያዊና ተራማጅ ኃይሎች ድጋፍ በነፃነት ትግሉ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጽዎ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ስለሆነም በዓለም ዓቀፋዊነት መንፈስ ከሶሻሊስት አገሮችና ከሌሎችም አብዮታዊ ኃይሎች ጋር የሚደረገውን መቀራረብና ግንኙነት ማህበራችን ይደግፋል”

/ትግላችን ዘና ቁጥር 1 ነሐሴ 69ዓ.ም. ገጽ 38 /



ለማሳየት የሞከርነው የውጭ እርዳታ ምንጊዜም ለተወሰኑ ችግሮች አጋዥ መሆኑን እንጂ ያሉብንን ያገሪቷን ችግሮች ሊያስወግድ ከቶ አለመቻሉን ነው፡፡ የችግሮቹ አመጣጥ ከአብዮቱ ሂደት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው አብዮቱ ጥሬ ፈር እንዲይዝ በነቃ፣ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝብ ትግል ጉዳና በተስለፋ ትግሉ ሺህ ጊዜ ረጅምና መራራ ይሁን እንጂ ዘላቂ መፍትሔዎች መገኘታቸው የማይቀር ነው፡፡ ሰፊውም ሕዝብ አንደ አንዱ ሰው ሆኖ ከተነሳና ችግሮቹን ራሱ በራሱ ከተጋፈጣቸው አየወደቀም ሆነ አየተነሳ ዕርዳታ በሚያስፈልገውም ወቅት የተመጽዋችነት ስሜት ባያድርበት ዕርዳታው ጊዜያዊ መፍትሔ፣ የአብዮቱ ድጋፍ እንጂ ወሳኝ አለመሆኑን አውቆ ሲጠቀምበት የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል ማለት ነው፡፡

የአብዮቱ ጉዳና በደንብ ያልተቀየሰለት ሕዝብ በፖለቲካ በኢኮኖሚ በሃገር መከላከል ደረጃም ቢሆን ከሌሎች ጥገኛ ከመሆን በስተቀር ሌላ ዕድል ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለሆነም በራስ መተማመን በሚለው አብዮታዊ መርህ ሰፊው ሕዝብ አንደ አንዱ ሰው እንዲንቀሳቀስ ማድረግና አብዮቱ ለፍትህ ለሰላም የመጣለት መሆኑን አውቆ አብዮቱን ራሱ ለቀፍ እንዲያካሂደውና ያለውን ሙሉ ኃይል በሚገባ እንዲረዳው ማድረግ የአብዮታዊያን ተግባር ነው፡፡ እንደደጋገምነው ጎታች ድርጅትና ትጥቅ በበለጠ መሟላት አለባቸው፡፡ እስካልተሟሉም ድረስ አብዮቱ ሳይገባዊና ትክክለኛ ፈር እንዲያስይዘው የተቀየሰው ብሄራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ፈሩን ለቦተና አብዮቱም ሲዉናገፍ ይችላል፡፡ በአጓሩ ዲሞክራቲክ አብዮት ሊሰለፋ የሚችሉ መደቦችና የመደቦች ክፍሎች ተበታትነው እንዲቀሩ ማድረግና ለቀበባሽ ኃይሎችም ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነው፡፡

በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ያለው ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት እንደ መሆኑ መጠን በመም እንደሚያመለክተው አብዮቱ ለዲሞክራሲና ለብሄራዊ ነፃነት የሚካሄድ አብዮት ነው፡፡ የአብዮቱ ኃይል ደግሞ ዘጠና በመቶ የሚያክለው ሰፊ ሕዝብ በመሆኑ ይህ ኃይል በሚገባ ከተባበረ በአንድነት ተነስቶ የሃገሩን ክብር ለማስጠበቅ ኢምፔሪያሊዝምን ለማባረርና የውጭ ተጽዕኖን ለማጥፋት በቂ ችሎታ ይኖረዋል፡፡

በተለይ ባሁኑ ጊዜ የውስጥና የውጭ አድሃሪዎች በአብዮታችን ላይ ከፋና በዘመቱበት ወቅት ሰፊው ሕዝብ በይበልጥ አብዮቱን እንዲያንከበክብ መደረግ አለበት፡፡ ሰፊው ሕዝብ ለአብዮቱ መቆሙን በየጊዜው አስመስክሯል፤ አሁንም በማስመስከር ላይ ነው፡፡ የአብዮታዊቱ እናት አገሩን ክብርና ሕልውና የተዳፈሩትን የመደብ ጠላቶችን በይበልጥ እንዲለይና እንዲቋቋማቸው ደግሞ በይበልጥ ዝግጁ እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡

በአራት ዓመት ትግል ሰፊው ሕዝብ የማይናቁ ድሎች እንዳገኘ ሁሉ
የማይናቁ ትምህርቶችም ቀስሟል:: በየጊዜው በአድኃሪው ቢሮክራሲ አማካይነት
የሚደርስበትን አሻጥርና ሴራዎች አንገሸገሸት " ቢሮክራሲ ይውደም"
" ቢሮክራሲ አይዘመት ይዘመትበት" እያለ ከዳር እስከ ዳር በስፋት እየተጋበ
ዟል:: ቢሮክራሲ የትግል መሣሪያም መሆኑን አውቆ በየጊዜው ቢሮክራሲን ይጠ
ይቃል:: ሆኖም ባሁኑ ወቅት ደርግና አስመሳይ ተራማጆች የያዙት አቋም የ
ሰፊውን ሕዝብ የመደብ ትግል ማፈን በመሆኑ የሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ትግል በ
ጣም ታውኳል:: ሰፊው ሕዝብ በአብዮቱ ላይ የደረሱበትን ችግሮች እንጥር
በሚገባ እንዳያውቅ ተገዷል::

እንዳንዱ ችግሮችን እናንሳ::

በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ ሶማሊያ ባላት የመስፋፋት ፖሊሲና
በዓለም ዓቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ትብብር ባደረገችው ወረራ ሳቢያ በዚህ አካባቢ
የሚገኙት ጭቁን ብሔረሰቦች ከፍ ያለ ችግር ላይ ወድቀዋል:: ባንድ በኩል
በወራሪው መንግሥት ወታደሮች በሌላ በኩል ደግሞ አዝማች በሆነው አድኃ
ሪው ሚሊቴሪ ቢሮክራሲና ተቀጥረው በመሰለላቸው ነፍጠኛ ተጨፈጨፉ:: ሁኔታው ሊ
ባባስ የቻለው፤በዚህ አካባቢ በሚኖሩት ጭቁን ብሔረሰቦች ላይ በተለይ ደርግ
<u>ዕምነት በማጣቱና</u> የብሄረሰቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት ከ
ሥራ ላይ ባለመዋሉ እንደሆነ ግልጽ ነው፤ በዚህ በፊት ተበዳዩን የማንቃት፣
የማደራጀትና የማስታጠቅ ተግባራቸውን ሲፈጽሙ የቆዩት አብዮታዊያን በቢሮክራሲ
አሻጥር በሥራ በመወገዳቸውና በመገደላቸው እንዲሁም ደርግ ቀለጥ ያለ የትምክ
ህተኛነት ፖለቲካ በመከተሉና እንዲስፋፋ በማድረጉ ነው:: እንዲሁም በዚህ አካ
ባቢ የዘመተው ሕዝባዊ ሠራዊት አባላት በብዛት ከሌላ አካባቢ የመጡ በመሆና ቸ
ው ብዙ ችግሮች አጋጥሟቸዋል :: አድኃሪ ሚሊቴሪና ሲቪል ቢሮክራቶችም አብዮ
ቱን ለማክሸፍ ከወራሪው ጋር በመተባበራቸው የአገሪቱ ክብርና ሕልውና ተደፈረ::
በሚገባ የአካባቢው ሕዝብ እንዲነቃ እንዲደራጅ እንዲታጠቅ ባለመደረጉ በሚ
ደርስበት ግፍ እልፍ አልፍ ወደ ፀረ አብዮት ሠፈር እንዲሰለፍ ሆኗል::ለሶማሊ
ያም ይህ ሁሉ ምቹ ሁኔታን ፈጠረላት የኢትዮጵያን ድንበር አልፋ አንዳንዱ ስፍ
ራዎችን እስከ 700 ኪሎ ሜትር በአንዳንዱ ስፍራ ደግሞ እስከ 350 ኪ.ሜ.
ለመያዝ በቃች::

እዚህ ላይ እንድንገነዘብ የሚያስፈልገው አስቀድሞ ደርግ በዚህ
አካባቢ በሚኖሩ ጭቁን ብሔረሰቦች ላይ <u>ፅኑ እምነት</u> ቢኖረው ኖሮና በሰበብ አስ
ባቡ ሚሊቴሪና ሲቪል ቢሮክራቶች በየሕዝቡ ድርጅቶች በሕዝባዊ ሠራዊቱና በጦር
ኃይሉ አመራር ባይሰገቡ ከፍ ያለ የፖለቲካ ቅስቀሳ በአካባቢው ቢካሄድ ኖሮ



ራሱ ያሰባሰበው ሕዝብ ጠላትን መክቶ ለመመለስ በበቃ ነበር! የአካባቢውም የሰ
ፊው ሕዝብ አብዮታዊ ትግል ወደ ኋላ ባልተጓተተ ነበር! የፖለቲካ ስህተት ላይ
በመወደቁም የአገሪቱ ክብርና ሕልውና ተደፈረ፤ ጦርነቱንም ለማካሄድ የውጭ
ዕርዳታ እንደ መሠረታዊ ጉዳይ ሆኖ ተወሰደ :: አሁንም ቢሆን በዚህ አካባቢ
ለተነሳው ችግር ጭቁኑ ሕዝብ በነቃ በተደራጀና በታጠቀ ሕዝባዊ ትግል ጎዳና
እንዲሰለፍ ካልተደረገ በውጭ ዕርዳታና ጦር የተገኘው ወታደራዊ ድል ከጊዜያዊ
ነት አያልፍም:: ችግሩ እንደገና ሊነሳና ሊባባስ ይችላል ማለት ነው::

በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይም በኤርትራ አካባቢ የተነሳው ችግር ከፖለ
ቲካው መፍትሄ ወታደራዊ መፍትሄ በመፈለጉ ደርግ ባሁኑ ጊዜ ወደደም ጠላ
በብዛት የኤርትራ ጭቁን ሕዝብ የተገንጣይ ቡድኖችን እየተከተለ ነው::
በዚህም ክፍለ ሃገር ለተነሳው ችግር የሚመጥን ፖለቲካና ሰላማዊ መፍትሔ እስካልተገ
ኘለት ድረስ ዘላቂ መፍትሔ አይኖርም:: በዚህም አካባቢ እንዲዘምት የተደረ
ገው ሠራዊት አብዮታዊ አመራር ማግኘት አለበት:: የሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥር
58. 21/10/69 በሚገባ እንዳስጠው " በዚያ መስክ የሚሰማራው ሠራ
ዊት፣በድርጊቶች በሚፈጥራቸው ግንኙነቶች ባጭሩ የኤርትራን ሰፊ ሕዝብ ዕምነት
ለማትረፍ የሚችል ለሰፊው ሕዝብ ደህንነት የሚንከባከብ እንጂ ወዳጁንና ጠላትን
ሳይለይ የማይመታ፣ቢቻልም ሰፊውን ሕዝብ የሚያነቃና የሚያደራጅ በዚሁ ሕዝብ
ሊታቀፍ የሚችል ሠራዊት መሆን ይኖርበታል::"

ባጠቃላይ የውስጥና የውጭ አድኃሪያን በአብዮታችን ላይ በሚያካሂዱት
ፀረ አብዮት ዘመቻ የደርግና አጋባዦች አቋም ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከችግ
ሩና ለውድቁ በመማር፤ ራሱን ችሎ አብዮቱን እንዲያፋፍም ሳይሆን ጊዜያዊ መፍት
ሔ በውጭ ዕርዳታና በጦር መሣሪያ ማግኘት ነው። ጉጉታቸውም ሰፊው ሕዝብ ለአ
ብዮቱ ያለውን ስሜት ለማቀዝቀዝ ነው:: አገራችንን ከችግሯ ለማዳን ሕዝቡ
ቆራጥ እንዳልሆነና ተደናቂ ታሪክ እንደሌለው ሁሉ የውጭ ወረራን ለመመከት የው
ጭ ዕርዳታን እንደ ወሳኝ ጥያቄ መወሰዱ አደገኛ መስመር ነው፤ሕዝቡን የፖለ
ቲካ ንቃት ሕሊና ከፍ ከማድረግ ይልቅ በውጭ ዕርዳታ ላይ ብቻ ማተኮር እስ
ከዛሬ ድረስ ነፃ ታሪካዊ የሆነች አገር እየተባለ ስትደነቅ የቆየችው ኢትዮጵያ
በባርነት ቀንበር ስር እንድትወድቅ ማገዝ እንዳይሆን ጉዳዩ በጣም አሳሳቢ
ሆኗል::

አብዮታዊያን ዕርዳታ ላይ ያላቸው አቋም የጠራ ነው:: ማህበራችን ያ
ለውን አቋም ከላይ ጠቅሰናል:: እስቲ ደግሞ የሰፊው ሕዝብ ድምፅ ቁ. 53/
15/7/69. እንጥቀሰው:—

“ በዓለም ዓቀፋዊነት መርሆ መሰረት የሚገኝ ዕርዳታ አስፈላጊ ይሁን እንጂ ለኢትዮጵያም ሆነ ለማንኛውም አገር ዋናው ነገር በራስ መተማመን ነው:: እርዳታ ድጋፍ እንጂ መሰረት አይሆንም ለእድገት ለሶሻሊዝም...ወዘተ ዋናው መሰረትና ዋስትና በራስ ኃይል መተማመንና ማንኛውንም ጉዳይ ከዚህ አንፃር መመልከት ነው:: ይህንን መረዳት ባንድ በኩል ያገሪቱን ክብርና ነፃነት ለጥቂት ጊዜያዊ ጥቅሞች ከመሸጥ በሌላ በኩል ደግሞ የሶሻሊስትና የሌሎችም አገሮች እርዳታ የኢትዮጵያ አብዮት ወሳኝ ጥያቄ አድርጎ ከመውሰድ ይጠብቀናል:: ”

እንግዲህ ምንጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ አስቀድሞ ራሱን በራሱ ችሎ አብዮቱን ማካሄድ ተገቢሩ ማድረግ አለበት:: አብዮት “ንግድ” ባለመሆኑ ካንዱ አገር የሚገዛ ወይም አንዱ አገር ለሌላው የሚያስተላልፈው ሸቀጥ ባለመሆኑ የአብዮቱ ወሳኝ ኃይል ምንጊዜም የአገሪቱ ሰፊው ሕዝብ ነው::

አንድ አብዮት ሂደቱ ፈጣን፣ደካማ፣ አጥቂ ወይም ተከላካይ የሚሆነው ካገሩ ካለው ተጨባጭ ሁኔታና አንድ መደቦች ኃይል አሰላለፍ ነው:: አብዮታዊያንም በየጊዜው ሰፊው ሕዝብ እንዲጠናከርና በመደብ ጠላቶቹ ላይ እንዲዘምትባቸው በተለይ ለሰፊው ሕዝብ ንቃተ ሕሊናውን ከፍ ለማድረግ፣በበለጠ እንዲንቀሳቀስ የዲሞክራሲን መብቶች አሁኑኑ መለቀቅ አጣዳፊ ነው: የሚሉት በዚህ አንፃር በመመልከት ነው:: ዲሞክራሲ አብዮቱን ለማፋፋም፣የአብዮቱ ሰፈርን ለመሰብሰብና ፀረ አብዮታዊያን ለማዳከም ይረዳል::

3. <u>በስ ውጭ ዕርዳታ ጉዳይ፣ራስን በራስ መቻልና ዓለም ዓቀፋዊነት አንዳንድ ነጥቦች</u>:

በሃገራችን በመካሄድ ላይ ያለው ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ቀንደኛ ጠላቶች ፊውዳሊዝም ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ሲሆኑ አብዮታችን ግቡን ለመታ የሚችለው ፀረ ሦስት የሆኑት ኃይሎች በሙሉ በፈርጅ በፈርጃቸውና በየደረጃቸው ተደራጅተው በነቃ፣በተደራጀና በታጠቀ ህዝብ አመጽ እነዚህን ሦስቱ ጠላቶች ሲደመስሱ ብቻ መሆኑ ተደጋግሞ ተገልጿል:: ከዚህ የትግል ፋና አስቶ በሌላ አማራጭ ወይም አቋራጭ አብዮቱን ከግቡ አደርሳለሁ የሚል ኃይል ሁሉ ከሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀድሞ በህዝብ ስም ስልጣኑንና ጥቅሙን ለማረጋገጥ የሚሻ ፀረ ሕዝብ ኃይል በመሆኑ የኢትዮጵያ ተራማጆች እስከመጨረሻው የደም ጠብታ ይዋጉታል:: በተጨማሪ የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የማይነጠል አካል እንደመሆኑ ሁሉ አጋዥ ኃይልና የሆኑ የተ



ባበረ የውጭ ጠላቶች እንዳሉት ሁሉ አጋዥ አስተማማኝ የሆኑ ወዳጆችም እንዳሉት አይካድም:: ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በተለይ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የጭቁን ሕዝቦችን ትግል ለማደናቀፍ በሚያደርገው ትግል በሃገር ውስጥ ያለውን ሰፊ ህዝብ ለረጅም ጊዜ አንቀሳቅሶ ለፀረ አብዮት ዓላማው ሊያውል አይችልም:: የውስጥ አድሃሪያኖችም እንደዚሁ ለቅልበሳ ዓላማቸው በሃገር ውስጥ ባለው ሰፊ ህዝብ ሊተማመኑ አይችሉም:: ስለሆነም በዓለም ዓቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና በውስጥ አድሃሪያኖች መካከል ያለው ፀረ አብዮት “ትብብር” የውጭውን ድጋፍ እንደወሳኝ የውስጡን ኃይል እንደ አጋዥ አድርጎ ለመውሰድ ይገደዳል::

በቪየትናም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምና የውስጥ አድሃሪያኖች ፀረ አብዮት “ትብብር” ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የአሜሪካ ወታደሮች ለማስገባት የተገደደው ለዚሁ ነው:: በአብዮቱ ሠፈር በዓለም ዓቀፋዊነት መንፈስና አብዮቱን ለማራመድ የሚደረግ ትብብር ግን ጨርሶ የተለየ ነው::በውስጥ ያለው የአብዮቱ ሠፈር በታሪክ ፈጣሪው ሰፊ ሕዝብ ዕምነት ያለው አብዮቱን ከግቡ ሊያደርስ የሚችለው ወሳኝኃይል የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ብቻ መሆኑን ያምናል::ወሳኝ ጉልበቱን ሕዝቡን ለማንቃት ለማደራጀት ለማስታጠቅ ባጭሩ አገሪቱን የአብዮት ምሽግ ለማድረግ ይፈልጋል:: ያለው ዓላማም አብዮታዊ እስከሆነ ድረስ ይህንኑ ያደርጋል:: በዚህም መንፈስ የዚህ አብዮት ዓለም አቀፍ ወዳጆች በፖለቲካ በዲፕሎማሲ በማቴሪያልና በሚሊተሪ የመርዳት ኃላፊነት ስላለባቸው ለጋራው ትግል ዕርዳታ ይሰጣሉ:: ነገር ግን ይህ ዕርዳታ በምንም ዓይነት የነቃ የተደራጀና የታጠቀውን ትግል ሂደት <u>የሚተካ</u> በሰፊው ህዝብ ቦታ አብዮት ከግብ አደርሳለሁ የሚል ዕርዳታ መሆን አይችልም:: ቪየትናም አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ የውጭ ወታደሮች ከዚህ ቁጥር በላይ የሚሆኑ የውስጥ አድሀሪ ወታደሮች የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ዘመናዊ የጦር ኃይል የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉልበት ተጭኗት በነበረበት የትግል ዘመኗ ጠላት ባየለ ቁጥር ሕዝቧን በይበልጥ ማንቃት ማደራጀትና ማስታጠቅን ባጭሩ ለአብዮቷ ወደፊት መገፋትን እንደመፍትሔ ወሰደች እንጂ የውጭ እርዳታን ትክክለኛ ከሆነው ከአጋዥነት ቦታ አንስታ ወደወሳኝነት ደረጃ አላስቀመጠችም:: አንድም የውጭ ወታደር አልተቀበለችም:: የቪየትናም አብዮት ግቡን የመታው ጀግናው የቪየትናም ሕዝብ የተደነቀ የአገር ፍቅር ታሪኩን አድሶ በዓለም ፊት ዘለዓለማዊ ተደናቂነትን ያገኘው በዚህ የተነሳ ነው:: ባጭሩ <u>የውጭን እርዳታ በወሳኝነት ደረጃ ማስቀመጥ</u> የሚገደዱ በህዝቡ ሊተማመኑ የማይችሉና የማይሹ ውለው አድረው በፀረ ሕዝብ ዓላማቸው የሚጋለጡ ኃይሎች ሲሆኑ ሃቀኛ አብዮታውያን የፈለገውን ረጅም ጊዜና መስዋዕትነት ከፍለው በነቃ፣በተደራጀና በታጠቀ ሕዝብ ትግል ይገፋሉ:: ያላቸው ህዝባዊና አብዮታዊ ዓላማ ህዝቡን ከማንቀሳቀስ፣ ከማደራጀትና ከማስታጠቅ እንዲያፈገፍጉ አያደርጋቸውም:: የውጭ እርዳታ የትግላቸው የማይነጠል አካል አድርገው ይቆጥሩታል:: ነገር ግን ምን ጊዜም ቢሆን አጋዥ እንጂ ወሳኝ አይደለም::

ይህ ከላይ የተጠቀሰው አቋም ''ራስን በራስ መቻል'' በሚለው መፈክር ስር ተወቃሉ የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች በይፋ የታገሉለት አቋም በጎራ መገለጫቸውና በድርጊት ፕሮግራማቸው ያፀደቁት መርህና ማህበራችንም በየንግግሮቹ ውሳኔዎቹ '' የውጭ ዕርዳታ አጋዥ እንጂ ወሳኝ አይደለም'' በማለት ያስተጋባው አብዮታዊና በእውነተኛ የወዝአደር ዓለም አቀፋዊነት ጋር ተጣምሮ የሚሄድ ማርክሲስት ሌኒኒስት አቋም ነው:: የድርጊቱ ፕሮግራም እንዲህ ይላል:: '' በራስ መተማመንና ራስን በራስ መቻል''በሚለው መርህ ወዛደሩ፣ ገበሬው ሕዝባዊ ሠራዊት፣ ወታደሩ ንዑስ ከበርቴውና አገር ወዳዱ ሀ/ ... ያለውን የመፍጠር ችሎታ በመጠቀም ከሚደርስበት ችግር ለመውጣት እንዲታገል መቀስቀስ ...'': የማህበራችን ውሳኔ ከላይ ስለጠቀስነው አንገመለሰበትም::

በዚህ ጥያቄ ላይ ማህበራችንና ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች '' ራስን በራስ መቻል'' በሚለው መፈክር ስር አጥብቀው በመሰለፋቸው በአንዳንድ አወናባጆች አካባቢ '' የውጭ ዕርዳታን ይቃወማሉ'' ዓለም ዓቀፋዊነትን ይቃወማሉ'' እስከማለት ተደርሷል:: ነገር ግን በተለይ ካለፈው መጋቢት 69 ዓ.ም ወዲህ በዚህ በውጭ ዕርዳታ ጉዳይ እየተፋፋመ የመጣው ክርክር ሆን ብለው ነገር በማጣመምና ስለኢትዮጵያ አብዮት፣ ስለ ሃገራችን ብሔራዊ ክብር ደንታ የሌላቸው ርካሾችና አገብጓጆች ከስተቀር ይዘቱ እጅግ ግልጽ ነው::

እንደማንኛውም ጥያቄ እነዚህ የአብዮት ጥያቄዎች መመለስ ያለባቸው ከመደቦች ትግል አንፃር ነው:: በነዚህ ጥያቄዎች ላይ የተለያዩ መደቦች የተለያዩ አቋሞች ይወስዳሉ::

አብዮታውያን ራስን በራስ መቻል በሚለው መርህ ቅድሚያ ይሰጣሉ:: ይህንን ማድረጋቸው ግን የውጭ ዕርዳታን መቃወማቸው ወይም ዓለም ዓቀፋዊነትን መሰረዛቸው አይደለም:: ሃቀኛ ዓለም ዓቀፋዊነት አብዮትን ለማራመድ የሚረዳ ዓለም አቀፋዊነት ብቻ ነው:: በዓለም ዓቀፋዊነት ስም የሚመጣ ዕርዳታ አብዮትን ሊያራምድ የሚችለው በአጋዥነት ደረጃ ሲሰለፍ ብቻ ነው:: የውጭ ዕርዳታን በወሳኝ ደረጃ ማሰለፍ ከተሞከረ አብዮትን ያደናቅፋል ዓለም ዓቀፋዊነትን ይፃረራል::

ቀልባሽ ኃይሎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ የውጭ ዕርዳታ እንዳይደርስ ይፈልጋሉ:: እነሱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕርዳታ እያስተባበሩና እያገኙ አብዮቱ ግን የነሱን ፀረ ህዝብ ህብረት ብቻውን እንዲጋፈጥ ይሞክራሉ::



በአብዮቱ ሠፈር ያሉት ግን የኢትዮጵያ አብዮት ከዓለም ዓቀፍ ወዳጆች ከሶሻሊስት አገሮችና ከሌሎች ተራማጅ ኃይሎች የፖለቲካ የዲፕሎማሲና የማቴሪያል ዕርዳታ እንደሚገኝ ይታገላሉ:: ነገር ግን በአብዮቱ ሠፈር ወዛደሩና ንዑስ ከበርቴው ስለዚህ ዕርዳታ አንድ ዓይነት አስተሳሰብ የላቸውም::

ማርክሲዝምና ንዑስ ከበርቴው ስለአብዮቱ ሂደት የተለያየ አስተሳሰብና አቋም አላቸው:: ስለሆነም ስለርዳታ ሚናም የተለያየ አቋም አላቸው::

የውጭ ዕርዳታ ጉዳይ በማርክሲስቶችና በንዑስ ከበርቴዎች መካከል በተጨባጭ ሁኔታ አከራካሪ እየሆነ የመጣው እነ ዓለማየሁ ኃይሌ ተደምስሰው አሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም በተለይ በውጭ ኃይሎች እየተጠቀመ አብዮታችንን ማጥቃት ከጀመረ ከአንድ ዓመት ወዲህ ነው:: የኢትዮጵያ ማሌዎች በሙሉ '' መሣሪያቸው ''ራስን በራስ መቻል ነው''

ይህ ማለት ግን የውጭ ዕርዳታ አያስፈልገም ማለት አልነበረም:: ሰህዱ ቁጥር 55 7/9/69 ዓ.ም. መኢሶን ከብሔራዊ ኮንፈረንሱ ላይ ካሣለፋቸው ውሳኔዎች ውስጥ እንዲህ የሚል ይገኝበታል::

'' በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች በዓለም ዓቀፍ ደረጃ የሚተባበሩበትን ያህል ተራማጅና ሶሻሊስት አገሮች አብዮትን ሊደግፉት መነሳታቸው ይታያል:: የኢትዮጵያ አብዮት ከዓለም ተራማጅና ሶሻሊስት አገሮችና ድርጅቶች የሚያገኘው ማንኛውም ዕርዳታ ለትግሉ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት እሙን ነው:: ነገር ግን መኢሶን የውጭ ዕርዳታን በሚመለከት በኩል ሁለት ነገሮችን መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ ያምናል:: አንደኛው የውጭ ሃይሎች ድጋፍ የዘቸን ኩሩና ታሪካዊ አገራችንን ብሔራዊ ክብርና ነፃነት የማይነካ ራሷን ለመቻል የምታደርገውን ጥረት የሚያግዝ እንጂ የማያደናቅፍ ርዳታ መሆን አለበት:: ሁለተኛ ማንኛውም ህዝብ በውጭ ርዳታ ላይ በመተማመን አብዮትን ከግቡ ለማድረስ እቸላለሁ በሎ ካሰበ ራሱን ማታለሉ ብቻ ሳይሆን አብዮቱንም ብሔራዊ ነፃነቱንም ያጣል:: ማንም ህዝብ በተለይም ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ኩሩና ባለታሪክ ህዝብ ከሆነ ለገዛ ነፃነቱ ለገዛ አብዮቱና ለገዛ ክብሩ ከሁሉም በፊት መተማመን ያለበት በራሱ መሆኑ መታወቅ አለበት:: ስለሆነም የውጭ ዕርዳታን በሚመለከት በኩል በብሔራዊ ክብርና ነፃነት እንደዚሁም ከሁሉ በፊት በራስ መተማመን የሚለው ዋናው መመሪያችን ይሆናል::''

ነገር ግን በጊዜው ደርግ በህዝቡ ሳይሆን በቢሮክራሲ ላይ መተማመን
ስለጀመረ የውጭ ዐርዳታንም እንደዚሁ የህዝቡን ትግል መተኪያና የሶበቀም አብ
ዮትን ፈር ማስያዣ አድርጎ ሊጠቀምበት ይቻላል ከሚል ተከበለና ገምቶ ነበር::
ህብረት መፍጠር የጀመሩት ደርግና ቢሮክራሲ በውጭ አርዳታ ተማምነው የነቃ፣
የተደራጀ የታጠቀ የህዝብ ትግልን ለመተካት እንዳይሞክሩ ነበር:: ንዑስ ከበር
ቴው ዝርዝር የሰፊውን ህዝብ ትግል ይፈራልና!
በተጨባጭ ሁኔታ ይህ ክርክር በተካ ከአንድ ዓመት በኋላ የውጭ ርዳ
ታ ባገራችን ከገባ በኋላ የምናየው ይህንኑ ነው:: ከውጭው ዕርዳታ መጨመ
ር ጋር ንዑስ ከበርቴው የህዝቡን ትግል ለመተካትና የራሱን ስልጣን ለማደላደ
ል ሞክሯል:: የተፈጠረው የደርግና የቢሮክራሲው ህብረት በዕርዳታው የነቃ
የተደራጀና የታጠቀ ህዝብ ትግልን ለማራመድ ሳይሆን እሱን ለመተካት እንደተጠ
ቀመበት አብዮታችን ከውስጥ ተቦርቡሮ ዛሬ የሚገኝበት አደገኛ ሁኔታ መድረሱ
ምስክር ነው:: በአሁኑ ወቅት ከ500 በላይ የሚሆኑ የመኢሶን አባላት በእስር
ላይ መገኘታቸው በመቶ የሚቆጠሩ የቀበሌ፣ የገበሬ የወዝአደር መሪዎች ተራማጅ
መለዮ ለባሾች አብዮታዊያን አገር ወዳድ የአየር ኃይል የምድር ጦር መኮንኖች
በእስር ላይ መገኘታቸውና የተራማጆችን ህብረት እንዳልነበረ አድርጎ የሚያወድ
ም ፀረ ቢሮክራሲ መንገብ የቀኝ ህብረት የውጭ እርዳታን ለነቃ ለተደራጀለታጠቀ
ህዝብ ዐመፅ መተኪያ ብቻ ሳይሆን ይህንን አብዮታዊ ፈር ለመለቀቂያ እንደተጠ
ቀመበት የሚያሳይ ነው:: ማህበራችንም ሆነ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች
በዚህ በኩል የነበራቸው ፍራቻ ከጥቂት ሰዎች አዕምሮ የፈለቀ ሳይሆን በኢትዮ
ጵያ ካለው የመደቦች አሰላለፍና ከንዑስ ከበርቴው መደብ ወላዋይነት ጠባይ የ
ፈለቀ ግምት እንደነበረ ለማየት አስቸጋሪ አይደለም::

ጥያቄው "የውጭ ዕርዳታ እንቀበል ወይስ አንቀበል? በሚለው ላይ አ
ይደለም:: አልነበረምም:: ክርክሩ የውጭ እርዳታ አጋዥ ነው? ወሳኝ? የውጭ ዕ
ርዳታ የነቃ የተደራጀና የታጠቀ ህዝብ ትግል ጉዳናን የሚያገዝ ነው፤ እሱን
የሚተካ? የውጭ ዕርዳታን የወላዋይ ንዑስ ከበርቴና አድሃሪው ቢሮክራሲ "የነቃ
የተደራጀና የታጠቀ ህዝብ ዓመጽ" የሚለውን ትክክለኛ የትግል ጉዳና ለመተካትና
ለመቀልበስ ሊገለገሉበት ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚለው ጥያቄ ነው:: ክርክ
ሩ የውጭ ዕርዳታን እንፈልግ አንፈልግ ሳይሆን አጠቃቀሙ ላይ ነው:: ወላዋዩ
ንዑስ ከበርቴና አድኃሪው ቢሮክራሲ የውጭ እርዳታን ወሳኝ አድርገው የህዝቡን
አብዮታዊ ትግል ተቀጥላ ለማድረግ ይታገላሉ:: አብዮታዊያን ደግሞ የውጭ ዕርዳ
ታ ህዝቡ ነቅቶና ተደራጅቶ ታጥቆ የሚያካሂደውን ትግል ማገዣ ያደርጉታል::
ይህ ልዩነት ሙሉ አድሮ በአብዮትና በፀረ አብዮት መካከል ያለ ልዩነት ይሆና
ል:: አብዮታዊያን የነቬትናምን ምሳሌ በመከተል የውጭ ዕርዳታን ለነቃ



ለተደራጀ ለታጠቀ ህዝብ አመጽ ረዳት እንጂ ምትክ እንዳይሆን የሚወተውቱና
እስካሁንም የወተወቱት ለዚህ ምክንያት እንጂ የውጭ ዕርዳታን በመቃወም፣ አያ
ስፈልግም ለማለት እንዳይደለ ግልጽ ነው::

ለማጠቃለል ያህል "በራስ መተማመን" "የውጭ ዕርዳታ ድጋፍ
እንጂ ወሳኝ አይደለም" አብዮታዊ መርህ ናቸው:: በራስ መተማመን የሚለው
የተመሰረተው በዓለም ዓቀፋዊነት ላይ ነው:: ሌኒን ሲጽፍ "ሃቀኛ ዓለም ዓ
ቀፋዊነት በርግጥ አንድ ዓይነት ብቻ ነው:: ይኸውም በራሳችን አገር ውስጥ
የሚካሄደውን አብዮታዊ እንቅስቃሴና አብዮታዊ ትግል እንዲዳብር በመስዋዕትነት
መታገል ይህንኑም ዓይነት ትግልና መስመር በሁሉም አገሮች ይካሄድ ዘንድ
/በፕሮፓጋንዳ በሞራል በቁሳቁስ/ መደገፍ" ነው ብሏል:: እንደገለፀነው ሃቀኛ
ዓለም ዓቀፋዊነት አብዮትን ለማራመድ የሚረዳ፣ እንደ አጋዥ ሆኖ የሚቀርብ
ዓለም ዓቀፋዊነት ብቻ ነው:: በተረፈ ሁልጊዜም የአብዮት ወሳኝ ኃይል ራሱ
ታሪክ ሰሪው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ተገንዝበን በነቃ በተደራጀ
ና በታጠቀ ሕዝባዊ ትግል ጉዳና የሚካሄደው አብዮታዊ ትግል ከዕለት ተዕለት
እንዲዳብርና አብዮታዊ መስመሩን እንዳይስት ማድረግ በአብዮታውያን ላይ የወደ
ቀ ከባድ ኃላፊነት ነው::

———///———

ቲ.ዘ.ዐ.ቲ

ከበዩከዳን ገረመው::

በውጭ ያሉ ተራማጆችም ሆኑ በአገር ቤት ያሉ ታጋዮች ዛሬ ደርግ በህብረተሰባችን መደብ አሰላለፍ ውስጥ የሚይዘውን ትክክለኛ ቦታ ማየትና ማሳየት ግዴታቸው ከመሆኑም በላይ ጊዜያዊ ተግባራቸው ነው እላለሁ::

ይህንን ስል ተራማጆች ለዚህ ጥያቄ እስከዛሬ መልስ ሳይሰጡ ቁር ተዋል ለማለት አይደለም:: በየጊዜውና በያጋጣሚው የኢትዮጵያ ተራማጆች ቢያንስ አብዮታዊ ክንፉ ስለዚህ ጥያቄ የጠራ መልስ ሰተዋል::

ዛሬ ይህንን ጥያቄ ላቀርብ ያስገደደኝ ሌላ ምክንያት አለ:: ሰሞኑን ስለደርግ የሰማኋቸው በደርግ ዘንድ ያየኋቸው ብዙ ብዙ ነገሮች ስጋት አሳድረውብኛል:: ባጭሩ የሰሞኑ ደርግ ነገረ ስራው አላማረኝም::

መቼም አንድ አብዮታዊ ይህንን በመሰለ መሰረታዊ ጥያቄ ስጋትና ጥርጣሬ ሲያድርበት ዝም ብሎ መቀመጥ ያስቸግረዋል:: ቢያንስ የተሰማው ጥርጣሬ በምን ላይ እንደሚመረኮዝ በግላዊ ስሜት ወይስ በነባራዊ ሁኔታ ብሎ ማሰላሰሉ አይቀርምና እኔም በነገሩ አሰብኩበት:: የሃሳቤን ቅደም ተከተልና ውጤት እንዲታወቅ ብዬ እነሆ ይህችን ደብዳቤ ሰኪላችኋለሁ::

እንግዲህ የደርግን መደባዊ አሰላለፍ እንደገና ማሰብ ያስፈለጋል ከተባለ በደርግ ዘንድ አዲስ አዝማሚያ አለ ማለት ነው:: ያንድ መንግሥት አዝማሚያ ደግሞ በተጨባጭ ድርጊቶች መመዘኑ አይቀርም:: እንግዲያውም ከፍ ብዬ ላቀረብኩት ጥያቄ አጥጋቢ መልስ መስጠት ካስፈለገ በግዴታ ከተጨባጭ ሁኔታዎች መነሳት አለብን:: ከግላዊ ገምት ላይ ተነስቶ የፖለቲካ እምነት መቀየስ ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ያለፉት አመታት በሚገባ አሳይተውናል:: ስለዚህም ከሁሉ አስቀድሞ የሰሞኑን የደርግ "አረማመድ" አይቶኛ የሚያደርጉትን ሁኔታዎች ለማስቀመጥ ወሰንኩ::

መጀመሪያ በሃሳቤ የመጣው ሰሞኑን ጋዜጦች ላይም ሆነ በጠቅላላ ባገሪቱ ሰው የሚከራከርበት፣ ከቅርብ ጊዜ አንስቶ ደግሞ ሰፊው ህዝብ በአንድ በኩል የመንግሥት ጋዜጦችና ቢሮክራቶች በሌላ በኩል ሆነው የሚከራከሩበት የዴሞክራሲ ጥያቄ ነው:: ነገሩ ብዙ ጥልቀት አለው:: ነገር ግን ጥልቀት ውስጥ ሳልገባ የታየኝን ለማስቀመጥ እሞክራለሁ::



እንዲያው በግርድፉ ለማስቀመጥ ያህል ባንድ በኩል "ዴሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ" የሚሉ አሉ:: በሌላ በኩል በዚህ መፈክር የማይስማሙ አሉ:: ግን እንግዲህ የሚያስደንቀው በዚህ ጥያቄ ላይ አለመስማማት መኖሩ አይደለም:: ትዝ ቢላችሁ በዲሞክራሲ ጥያቄ የአህአፓን ምሁራን "እነ ሃማኛ እነማርታ ዋለልኝን አስረድተን እንከርክረን ጉዳዩን ወርሰነው ነበር:: የክርክራችን ነጥቦች "ዲሞክራሲ ለማ? ዲሞክራሲ መቼ? ዲሞክራሲ ለምን?" የሚሉ ነበሩ:: ይገርማችሁ የዘንድሮውም ልዩነቶች እነዚው ናቸው:: አንስማማም ባዮች ደግሞ አብረን ኢህአፓን ካሸነፍነው ማህል የተወጣጡ ቡድኖች ናቸው:: ምን እንደገናቸው ምን እንዳገኙ በበኩሌ አልገባኝም:: ወደፊት ይገለፅልኝ ይሆናል::

የሆነው ሆኖ በግዴ ተስማሙ ማለት ያስቸግራልና ያለተስማሙበትን ምክንያት ወደ ማጤኑ ተሸጋገርኩ::

ከውስጣቸው እንዳንዶቹ "አሁኑኑ" የምትለዋን አባባል አይቀበሉዋትም:: ግን ደግሞ ዴሞክራሲ አሁኑኑ ቢገኝ ክፋቱ የት ላይ እንደሆነ አያስረዱም:: በግድ ሲያፋጥጧቸው "አድሃሪው ስለሚጠቀምበት" ይላሉ:: ግን ይህ ክርክር የማያዋጣ በመሆኑ፣ ዴሞክራሲ የሚገኘው በትግል ስለሆነ አሁኑኑ ብሎ ከመጠየቅ "ዲሞክራሲ በትግላችን" ማለትን ይመርጣሉ:: አሁኑኑ ባዮቹም የሚሉት ዲሞክራሲ አሁኑኑ እንዲለቀቅ እንታገል ስለሆነ ክርክሩ ተመልሶ "አሁኑኑ" መባሉ ምን ክፋት አለው ወደ ሚለው ያሸቀለቅላል:: ያኔ ደግሞ በትግላችን ባዮቹ መልስ አይሰጡም::

በበኩሌ ለነገሩ እነዚህ "ጉበዝ" ታጋዮች "እነማን ናቸው ብዬ ከማጠያየቅ ለቆጠብ አልቻልኩም:: ያገኘሁት መልስ እጅግ ግራ አጋብቶኛል:: "ታጋዮቻችን" ለካስ በዚህ ጥያቄ ከደርግ ጋር ሙሉ በሙሉ የተሰለፉ ናቸው:: እኔማ በትግላችን የሚለው ቃል ካልገባ ብለው ሲከራከሩ ከመንግሥት ጋር ከፋኛ ትግል የገጠሙ መስሎኝ ነበር:: አሁን ግን "አሁኑኑ" የምትለዋ ቃል እንድትወጣ መከራከራቸው መሆኑን ተረዳሁት:: ደርግም ቢሆን ደግሞ እኔ እስከማውቀው ድረስ ዴሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ አለሰጥም ብሎ ይፋን ያህል ትግል ሲጠይቅ ትዝ አይለኝም:: ያስቸገረት የደርግ ቀኝ ክንፍ የሚባሉ ነበሩ:: እነሱም ቀጋቸውን አገኙተዋል:: እንዲያውም ሰባት የደርግ አባሎች በተረሸኑ በማግስቱ ኮሎኔል መንግሥቱ አብዮት አደባባይ ላይ ሆነው "ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ በስፋት ይታወጃል" ሲሉ እስከነፈገግታቸው ትዝ ይለኛል:: መቀየት ደግ ነው:: ዛሬ ርዕሰ ብሄሯም ወጓጆቻቸውም ዲሞክራሲ በትግላችን እንቀዳጃለን እያሉ ትዝብት ላይ ጣሉን "አውሳሳ ሜዳ ላይ የቆመ ሰው ፀጉሩን በእጁ ይዞ ሰውነቱን ከምድር ከፍ ለማድረግ ከራሱ ጋር ሲታገል ነቅ ታየኝ" ሲል ያስፈራት አንድ የሲኒን ምሳሌ ትዝ አለችኝ::

ለማገናኘትም በመጀመሪያ በሃሳቤ የመጣው አለቆች ያለኝ ቀን ኋላ ዞር ይህ የሚመከራቢ ጥያቄ ነው::

በዚያ ብዙ ሁኔታዎች በሃሳቤ መጡ:: ያኔ በደጉ ዘመን መስጊድ እንደገባች ወንድ ያባረርናቸው አድሃሪ የጦር መኮንኖች "አርቂዎች" ስለሆኑ በታቸው ተመለስቀል ተባሰን:: እነተፈሪ በንቲና እነለማየሁ ሃይሌ " ጌዜ" ጣላቸው እንጂ እንደዛሬ ቢሆንማ " አርቂቶታቸው" በደፋ ተነገርላቸው ይቀርታ ይደረግላቸው ነበር! እንቢን እነሱ፤ የደቀቁን ህዝብ ቢበዘበዙ የቀቁ ነፍጠኞች " ለሶማሌ መውሃኔት እና ነን" እያሉ ትጥቃቸው ተመለስላቸዋል:: እነዚያም የሚሉት ቅራኔያችንን አቻችለን ሱማንን እናጥቃ ነበር:: ደርግም ዛሬ ይህንኑ ብሎ ነፍጠኛ እያስታጠቀ ገበሬን ትጥቅ ያስፈታል:: ሰሞኑን ብዙ የቀበሌ ተመራጮች ያለቃሉ:: በወደቀት ፈንታ ህዝቡ ለሚመርጣቸው ወኪሎች ይተኩሉ፡ብለን ስንጠብቅ ለካ ደርግ የህዝቡን ተመራጮች ገለል ለማድረግ ራሱ ያስገደላቸው ይመስል በራሱ ኃለበት የታወቀ ቢሮክራቶችን በተመራጮች ፈንታ እንዲተኩ አደረገ:: በደርግ አረማመድ ላይ ያደረብኝ ጥርጣሬ በገላጭ ሰማት ሳይሆን ከነባራዊ ሁኔታ የመነጨ ጥርጣሬ መሆኑን ተገንዝቢያለሁ::

ለምን ደርግ አዝማሚያውን ቀየረ ብዬ ባሰላስል"ስለጣኑን ለማደላደል ነው የሚለው መልስ ብቻውን በቂ ሆኖ አላገኘሁትም:: ባለፋት አመታት በመጠኑም ቢሆን የፖለቲካ ትምህርት አግኝተናልና በቀሰምኩት ትምህርት ተጠቅሜ ምርምሬን ለገፋበት ወሰንኩ:: ከሁሉ አስቀድሜ ስለ መደቦች ጠባይ በዝርዝር የሚያትቱ መፅሃፍት ፈልጌ በተለይ ስለ ንዑስ ከበርቴ መደብ በደንብ ለማወቅ ንባብ ጀመርኩኝ::ኃደኞቹ ንባብ ጠቃሚ ነው:: በውነቱ ለቀረበልኝ ጥያቄ በቂ መልስ አገኘሁ ለማለት ይቻላል:: ካነበብኳቸው መፅሃፍት አንዱን ልጥቀስላችሁ:: ማርክስ " መደብ ትግል በፈረንሳይ" በሚለው መፅሐፉ ላይ ስለ ንዑስ ከበርቴ ሲያትት እንዲህ ይላል::

"...ሚያዝያ 16 ከበርቴው ጋር አበረ:: በሰኔ ወር ከወዛደሩ ጉን ሆነው ታግለው ነበር:: ይህንንም በማድረግ ፓርቲያቸውን ጠንካራ የሚያደርገውን ደጀን አፈረሱት ምክንያቱም ንዑስ ከበርቴ በከበርቴው ላይ አብዮታዊ አመለካከት የሚኖረው ወዛደሩ ከጀርባው እስካለ ድረስ ብቻ ነውና:: ሆኖም ዋጋቸውን አገኙ:: ...ተገቢው ዋጋ ሳይሰጣቸው የከበርቴው ተቀጢላ ሆኑ:: ከከበርቴው ቀንጢት ፍርፋሪ ሊያገኙ አልቻሉም::"

የደርግ አዝማሚያ እንግዲህ ሚስጥሩ እዚህ ላይ ነው:: ምን ቢባል?የመደብ ጠባይ:: በበኩሌ ከዚህ የተረዳሁት ሁለት መልክት አለ::



ባጭሩ እነዚህን ሁለት መልዕክቶች ለማስቀመጥ እሞክራለሁ:: <u>አንደኛ መልክት</u> ደርግ የንዑስ ከበርቴውን መደብ እንደመወከሉ መጠን ወዛደሩና ሰፊው ገበሬ ከጀርባው በነበረ ዘመን በባላባቶችና በቢሮ ከበርቴው መደብ ላይ አብዮታዊ አመለካከት ነበረው:: ተራማጆች በዚህ በኩል ብዙ ፅፈዋል:: እኔም ምሳሌ ጥቀስ ብባል የመሬት አዋጁ እላለሁ:: ሌላስ ቢባል ደርግ በነተፈሪ በንቲ በነትስፋዬ ታደሰ ላይ የወሰደውን እርምጃ እጠቅሳለሁ:: በዚህ አገባብ ከማርክስ ጥቅስ ያገኘሁት ትምህርት እውነተኛ እነዚያ አናርኪስቶች ቃገም እንዳላገባቸው አረጋግጦልኛል:: ደርግ ተራማጅ እርምጃዎች መውሰዱ ከመደብ ጠባዩ ሲታይ አያስደንቅም::

<u>ሁለተኛ መልክት</u>: ሁለተኛው መልክት የሰሞኑን የደርግ አዝማሚያ የሚመለከት ነው:: ደርግ የንዑስ ከበርቴውን መደብ እንደመወከሉ መጠን ወዛደሩና ሰፊው ገበሬ ከጀርባው ሲጠናከርበት ሊቀድመውና የትግሉን አመራር ለመውሰድ ሲያጣው ተደናግጦ ወደ ፀረ ህዝቡ ቢሮ ከበርቴ መቀራረብን መረጠ:: እውነትም ታዲያ ነገሩን ጠጋ ብለን ስናየው ደርግ ከቢሮ ከበርቴው ጋር ማበር የጀመረው በሚያዝያ የሰራተኞች ቀን አከባበር ወዛደሩ ባሳየው ከፍተኛ ጥንካሬ ወቅት ነው:: አሁንም ቢሆን የዛሬው የደርግ አረማመድ ከመደብ ጠባዩ አንፃር ሲታይ ያስደንቃል ለማለት ያስቸግራል:: የቀን ኋላ ዞሩን ተርጉም መደባዊ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም::

ግን ይህ ሁሉ ሆኖ

ባለ አሁንም ቢሆን በቂ መልስ አገኘሁ ብዬ ለመናገር ያስቸግረኛል:: በመጠኑም ቢሆን የምትከነክነኝ አንድ ነጥብ አለች:: ከፍ ብዬ ከጠቀስኳቸው ነጥቦች ተነስቼ የደርግ ነገር አከተመ አለቀ ደቀቀ ብዬ አፌን ሞልቼ እንዳልናገር አሁንም ቢሆን የደርግ ጋዜጦች አብዮት በሸለዝም፤የነፃ የተደራጀ የታጠቀ ትግል ወዘተ.... ይላሉ:: ይህ ብቻ ሳይሆን የወዛደር ፓርቲ መቋቋም አለበት እየተባለ በደፋ ይነገራል:: እውነትም ደርግ ጓዙን ጠቅሎ የህዝቡን ወገን ጥሎ ሄዷል ከተባለ ለምን እስከናካቴው በግልፅ አይናገርም ብዬ ራሴን መጠየቅ ግድ ሆነብኝ:: በውነቱ ለዚህ ጥያቄ መልስ ማግኘት ብዙም አላስቸገረኝ ነገሩን ጠጋ ብዬ ሳየው ኢህአፖም ሆነ ተፈሪ በንቲ ሲሳይ ሀብቴም ሆነ ጌታቸው ናደው የቀለበሳ ሙከራ ባደረጉበት ጊዜ ባነጋገር ደረጃ ሁሉም ተራማጆች ነበሩ:: እውነትም ታዲያ ትግሉ እስተገታ ድረስ የደገፉው ጋጋታ አድሃሪያቸን ብዙም አያስጋቸውም:: ነገሩ ለካ " የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው" ነው::ይልቅስ ያመራመረኝ የወዛደር ፓርቲ ጥያቄ ናት በውነቱ ያሰጋኝ ፓርቲው የወዛደር መባሉና አለመባሉ አይደለም:: ያጠራሪ ነገር ብዙም ዋጋ የለውምከና ብዬ ተረድቻለሁ:: ደግሞ ባገራችን " መልክ ጥፉ በስም ይደገፉ" የምትባል ተረት አለች:: ዋና ነገሩ የታየኝ ፓርቲ ማቋቋሙ ላይ ነው:: የሚቋቋመው ፓርቲ በስም ሳይሆን <u>በድርጊት የወዛደሩን ጥቅም የሚጠብቅ ነው ወይ</u>? መቼም እኔ እስከማውቀው አንድ ፓርቲ ሃቀኛ የወዛደር ፓርቲ እንዲሆን ሁለት ነገሮች መሟላት አለባቸው:: አንደኛ በማርክሲስት ሌኒኒስቶች ማህበር የርዕዮታለም ትግል ተደርጎ በጠራ መስመር ላይ አንድነታቸው መገንባት አለበት::

ሁለተኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በወዝደሩ ዘንድ በሚያደርጉት ቅስቀሳና በሚሰጡት ትምህርት ከመደቡ ጋር በሚገባ መዋሃድ አለባቸው።በኋላ በሚቋቋመው ግንባርም የወዝደሩ ፓርቲ አመራሩን እንዲይዝ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች በህዝባዊ ድርጅቶች ዘንድ ያደራጁና የመሪ ሚና መጫወት አለባቸው:: ህዝባዊ ድርጅቶችም ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ መስራት አለባቸው:: በውነቱ ደርግ ስልጣኑ በቅ እንደመሆኑ መጠን ይህንን ሁሉ ተግባር ለማቃለል ግዴታም ችሎታም ነበረው::ግን ዛሬ የሚታየው የተገላቢጦሽ ነው:: በማሌያኖች መሀከል ውይይት እንዲካሄድ የዲሞክራሲን መብቶች፤ ከራሳቸው ጋር ታግለው አለዉረሰም መሰለኝ፤አሁንም አልታወቁም:: ማሌያኖች በወዝደሩ ዘንድ ቅስቀሳ ሲያካሂዱ ሲታሰሩ ሲገረፉ አየን:: የሚፈቀዱላቸው አንዳንድ ቡድኖች ብቻ ናቸው።እነሱ ደግሞ የዲሞክራሲ መታወቁና የህዝባዊ ድርጅቶች በዲሞክራሲያዊ መንገድ መጠናከር አጀንዳ ያሳሰባቸው አይደሉም::

ደርግ ሊፈጥር ያሰበው የወዝደር ፓርቲ እኔ እንደገባኝ የሚቋቋመው ህዝባዊ ድርጅቶችን ከላይ በኀይም በውድም በመቆጣጠር "ከሰቀለቅ" ቡድኖች ማህል ለያስመላ ክርክር በማካሄድ / እስከ ዛሬ የክርክሩ ነጥብ ምን እንደሆነ በበኩሌ አላውቅም/ ከዛም ውህደት ተፈጠረ ብሎ የወዝደር ፓርቲ ይሸውለናቸው በማለት ሳይሆን አይቀርም:: በተለይ ከፍ ብዬ ከጠቀስኩት የደርግና የቢሮክራቶቹ መቀራረብ ጋር ባንድነት ስመዝነው የዚህ ፓርቲ ነገር ፍፁም አላማረኝም:: ያንዱ ቢሮክራሲያዊ ስልጣን መደላደልን የሚያመጣ መስለኛል።መቼም ደርግ አሁን የደመረውን አዝማምያ ቀጥሎ ከአብዮቱ ይልቅ ስልጣኑን ማደላደል ከመረጠ አብዮታችን ከፋኛ ችግር ውስጥ መውደቁ አይቀርም እላለሁ:: ደርግ ከቢሮክራሲው ጋር ተዋህዶ ከተደላደለ፤እንግዲ የወዝደሩና የገበሬው ጥቅም ሊጠበቅ ቀርቶ ያ የፈረደበት የንዑስ ከበርቴ መደብ እንኳ ማርክስ እንዳለው ከቢሮ ከበርቴ "ፍርፋሪ" አያገኝም::

እነዚ "ፊዳሊቶች" ገና በሰበበቱ ጊዜ "የደርግ ታሪካዊ ሚና የተወሰነ ነው" ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ ዛሬ ገና ገባኝ::

ለካስ እነሱ ነገሩ ገብቶዋቸው ተዘጋጅተውለት ነበር::ዛሬ ደርግ ወደ ቀኝ ሲል እነሱ ወደ ህቡዕ ገቡ:: እንደውነቱ ከሆነ እነሱ ህቡዕ የገቡ ሰሞን እኔም "የፈረጠጡ" መሰሎኝ ሆድ ብሶኝ ነበር:: ዛሬ ነገሩን ሳሰበው ፈርጣጩ ሌላ ሆኖ አገኘሁት:: "ያበዱን አክክ ለምዶ" የምትለዋ ተረት ትዝ አለችኝ:: በዛን ሰሞን እንደሰማሁት ከሆነ ደርግ አንዳንዶቹን ደርሶባቸው ታስረው በቃይ አያቶ ነው ይባላል:: ደርግ በይፋ ተባስተናል በሉ በሉ፤እነሱ ፍንኮች አለል ብለው እየታደኑ የተገደሉ ብዙ ናቸው:: ግን ድርጅታቸው ብዙ ተቀባይነት ያለው መሰለኝ የደርግ ካድሬዎች በየሲሚናሩ በየፋብሪካው በየቀበሌ የገበሬ ማህበራት እነሷቸውን ለማሳጣት ፍዳቸውን አያዩ ናቸው:: በቀደም ለት የመኢሶማ የሸዋ ክፍለ ሃገር ገበሬ ማህበራትና የአዲስ አበባ የቀበሌ ማህበራት ያሳለፉትን ውሳኔ በበራሪ ወረቀት አይቼ በአዲስ ዘመን ደርግ አጫዉ ነው ያወጣው የሚል ወሬ በለሰማሁ ባስተያየው እውነትም ደርግ እንደሸወደን ተረዳሁ::



ደርጎች በሚያቀርቡባቸው ክሶች ትዝ የሚለኝ "እናት አገራችን ተወራ ባለ ፈረጠጣችሁ" የሚለው ነው:: እነሱ የሚሉት አብዮታችንን እያጠናከርን ካለሆነ አብዮታችንን ከወራሪ ለናድን አንችልም ነው::በደርግ በነሱ ማህል ያለው ልዩነት እናት አገር ማዳን ወይስ አብዮታዊት እናት አገር ማዳን የሚለው ነው ይባላል:: እኔ በበኩሌ የነሱ አቋም ትክክል መሰለኝ:: ዋና ነገሩ አብዮትንም እናት አገርንም መጠበቅ ነው:: ደግሞ የሲማሊን ወረራ ለማባረር የኡጋዴንን ጭቁን ህዝቦች በነፃነትና በማስመታት ረገ የሚኪድ አይመስለኝም:: ይልቅስ የኡጋዴንን ጭቁን ህዝብ መብት ጠብቆ/ ነፃነቱን አክብሮ/ በህዝቡ ላይ ተመርኩዞ ለወራሪው መሰረት ማሳጣት በይበልጥ ጠቃሚ ይመስለኛል: በመሳሪያ ጋጋታ በነፃነት ድጋፍ የሲማሊን ወራሪ ማባረር እስከምን አብዮትን እንደሚያጠናክር እስካሁን ለረዳው አልቻልኩም:: ግን የሚገረፉትና የሚታሰሩት እንዲፈቱ ብዙ ህዝባዊ ድርጅቶች ጥያቄ አቅርበዋል ይባላል:: ደርግ ስለዚህ ጉዳይ ምን መልስ እንደሰጠ አላውቅም:: የታሰሩት ግን እስካሁን እንዳልተፈቱ አውቃለሁ፤እንዲያውም እኔ እንደገባኝ ከሆነ ህቡዕ የገቡትን ወይንም እነሱን ይደግፋሉ እየተባሉ የሚጠረጠሩትን ማሳደዱ ቀጥለዋል:: እንዲያውም በሚስጥር ይገደላሉ::

እንዳደሉ ረቂቅ ነው:: በህዝብ የሚታወቁትን የቀበሌ ማህበራት መሪዎች የወዝደር ተወካዮች ወዘተ "ሰውር ቀጥር ነፍስ ገዳዮች" ይገድሏቸዋል ኢህአፓ አስገደላቸው እየተባለ አብዮታዊ ተብለው ይቀበራሉ::ይገርማል የሰውን አድርስ የአዘ አንባ ማፍሰስ ይፈቻሃል ይኼ ነው:: በህዝብ ያልታወቁት ደግሞ ይገደሉና፤ አናርኪስቶች ናቸው ይባላሉ:: ምን አለፋችሁ እነዚህ ጓዶች ባንድ በኩል "ኢህአፓ" ሲገድሏቸው በሌላ በኩል "ኢህአፓ" ተብለው ሲገደሉ በማህል ብዙ ታጋዮች አለቀዋል:: በስመ ቀይ ሽብር ብዙ ግፍ እየተፈፀመ ነው:: አብዮታዊያን ታጋይ ቀበሌ ማህበራትና የጥበቃ ጓዶች በትጋት በሚያካሂዱት እውነተኛና ተገቢ ቀይ ሽብር አጠገብ ደርግ ቀይነቱ በጣም አጠራጣሪ የሆነ ተቃራኒ ነጭ ሽብር በማካሄድ ላይ ነው:: ደርግና አዉሃሪው ቢሮክራሲ በሚያካሂዱት ነጭ ሽብር ተበሳጭተን እውነተኛውን ቀይ ሽብር እንዳናጥላላ፤በሌላ በኩል ደግሞ በእውነተኛው ቀይ ሽብር እየተሸፈነ የሚካሄደውን ነጭ ሽብር ከማውገዝ እንዳንቆጠብ ብዙ ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ይመስለኛል::

ለማጠቃለል ያህል በተራማጅ ስም ብዙ ብዙ ገፎች እየተፈፀሙ ነው:: አንዳንዱ ጓዶች ምናልባት ይህን ስታነቡ ደርግን ያላግባብ የከሰስኩ ይመስላችሁ ይሆናል:: አይምሰላችሁ የደርግ ነገር አላማረኝም:: መቼም ደርግ ወደ ሰፊው ህዝብ ሰፈር ገብቶ ደስ ብሎኝ ነበር:: አንዳንዶች ቀኖች መጥፎ አይደሉም:: ግን የዛሬው አዝማሚያ ከቀጠለ ምኞታችን የህልም እንጀራ እንዳይሆን ፈራሁ:: በትግሉ ሜዳ ደግሞ የህልም እንጀራን የመሰለ ከፋ ነገር የለም:: በበኩሌ የመጣው በመጣ እና በህዝቡ ጎን ምን ጊዜም መቆም አለብን እላለሁ:: በርጋታና በትጋት የደርግንም ሆነ ጠቅላላውን ሁኔታ መርምረን ለተጨባጩ ሁኔታ ተጨባጭ መፍትሄ መተለም ተገቢ ይመስለኛል::

በኔ ግምት አሁንም አሳማችን ለክ በብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም እንደሰፈረው ሳናወላውል ለዲሞክራሲና ለብሄራዊ ነፃነታችን መታገል ነው:: ዲሞክራሲ ማለት ዛሬ በመጤናከር ላይ ያለው ቢሮክራሲ የሚደመሰሰበት ህዝባዊ ድርጅቶች አበበው ወደ የህዝባዊ ስልጣን አውታሮች የሚለወጡበት ያገራችን ፖለቲካ በህዝብና ለህዝቡ የሚወሰንበት ስርዓት ነው:: ብሄራዊ ነፃነት ደግሞ አገራችን ሃብትዋንና ምርትዋን ለህዝቦችዋ የምታውልበት ፓለቲካዋን ያለማንም ተፅዕኖ የምትወስንበት አገራችን የማንም የጦር ሃይል መስፈሪያ የማትሆንበት ሁኔታ ሲሟላ ነው:: ደግሞ ለደቂቃም ለገዛ ነጋው የማያስፈልገው ይህንን ሁሉ ትግል በራሳችንና በህዝባችን ላይ ተማምነን እንጂ በማንም ወዳጅ ላይ ተማምነን አለመሆኑን ነው::

ጓዶች አብዮታችን ከፋ የቀለበሳ ደመና አለብሰዋታል:: ነገ ደግሞ ከበረታን እናሸንፋለን::

ጓዳዊ ሰላምታ ይድረሳችሁ

የናንተው



**ከ30|1|78 — 2|2|78 በሞስኮ ከተማ የተደረገው**

**14ኛ የሶቭየት ህብረት የኢት.ተ.ባ. ዋለቂ ጉባኤ::**

የኢትዮጵያ ህዝቦች በወሳኝነቱ ላይ በአንድነት እንቅስቃሴ ከነበረበት ከየካቲት 66 ጀምሮ የተጓዘበት አብዮታዊ ጉዞና አሁን ውስብስብና መዝግዛዝ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው:: ለዚህ የትግል ጉዞና ቀርጊያ የሚከፍተ ከሃሊ ሃይሎችን ተገናኙሰል:: በዚህ በአጭር ጊዜ በከኙው መራራ ትግል ለወሰኙ ወደፊት ለሚወበቀት ዉሎች የሚረቱት ብዙ ትምህርቶች ተበዝተዋል:: ወደፊትም በሚያደርገው ትግል ከዚህ የበለጠ ትምህርቶች እንደሚቀስሙ አያጠራጥርም::

የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮት በዚች አጭር እድሜ ውስጥ ብዙ የመደብ መገሸረቆቶች ታይተውበታል:: የውስጥና የውጭ ሃይሎች ያሳነዳች ማጋደቂ ተፈታትነውታል:: በየጊዜው የተነሳበት ወሳኞች ብዙ ጉዳቶች አድርሰውበታል:: አብዮትን ከቀልበስ ለማዳንና የአገሪቱን ህልውና ለማስጠበቅ በየፊቀነት ሲታገሉ ብዙ አርበ አደሮች፣ ወዝአደሮች፣ አብዮታዊያን ምሁራን፣ ሴቶች፣ ወጣቶችና መለዮ ለባሾች በየቦታው ወድቀዋል:: ወሳኝ በአብዮቱ ላይ ጥቃት ያደርሰበት እንጂ በዚህ ጥቃትና ጉዳ አብዮትን ለመቀልበስ አልቻሉም:: እንዲያውም በሬው ህዝብ ወሳኞች በየጊዜው በደረሰበት ጥቃት ወበበ ኢ.የተመናኩረና በየፊቀነት የመደብ ትግሉን እያፋፋመ ሄደ እንጂ ለአድሃሪያዎች ጥቃት ተበገሮ ትቂን በመናታት አብዮትን አሳልፎ አልሰጠም::

የኢት አብዮት ከተጀመረ አንስቶ ብዙ ወሳኞች በየጊዜው እንደተነሱበትና ብዙ የመደብ መገሸረቆቶች እንደታየበት ይታወቃል:: አብዮቱ በዚህ በአጭር እድሜው ውስጥ አቀቂነትና ተከሳካይነት ተፈራርቆበታል:: ሆኖም የኢት አብዮት ከአቀቂነት ወደ ተከሳካይነት ከሸገሸገበት ከመጋቢት 69 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ የትግል ምእራፍ ውስጥ ይገኛል:: አንድ ዓመት ባልሞላው ጊዜ ውስጥ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት ብዙ ሃይሎች ከአብዮቱ በፊት በመሸሽ ላይ ይገኛሉ: በሶ ተፈፃሚ ለነፃ፣ ለተደራጀና ለታወቀ ህዝባዊ አመጽ አያሉ ቢያስተጋቡ የነበረው ዛሬ መፈክሩ ወደ ሥራ ይተርጉም ቢባል ወገቢን ማለት ጀምሯል:: ትናንት የተፈፃሚዎች አንድነት ይወነክር፣አብዮትን ለማረመድ ዲሞክራሲ በአስቸኳይ፣ ቢሮክራሲው ይደምሰስ፣ የአዲስ ፕሮግራም በበራ ሳይ ይዋል እያሉ በበሬው ህዝብና በተፈፃሚ በፊር በያገኙበት የነበሩት፣ ዛሬ ተፈፃሚዎችን በየቦታው እያሳደዱ ማሰር፣ ማሰቃየትና መግደል ይዘዋል፣ 'ዲሞክራሲ በትግል' ማለት ጀምረዋል:: ትናንት ቢሮክራሲው ይውደም እንዳላሉ ዛሬ 'ቢሮክራሲው በይፋር አብዮቱ ወደፊት ቢልገፋ ነበር የወጧለትን አድሃሪና የህዝብ ወሳኝ ቢሮክራሲው ለአብዮቱ ለመቀቀም ይችላል በማለት ከዚህ ከአብዮቱ አቢይ ወሳኝ ጋር ግንባር ፈጥሮ በአብዮቱ ላይ ከፍተኛ የቀልበሳ ስራ ያካሂዳሉ:: ትናንት የኢህአፓን ነጭ ሽብር እንቃወማለን የሚሉት ዛሬ በኢህአፖ አዋቀበሉ ሃቀኛ ተፈፃሚዎች ላይ ዘምተዋል:: ትናንት በአብዮቱ አደባባይ ለበሬው ህዝብ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ነን በለው ያበዉቀት በደፍ፣ ወዝና ጫሌሪያ ዛሬ የአዲስ ፕሮግራም በመክዳት ላይ ይገኛሉ::

በዚህ በፊት ከነአለማቸው ላይ ህዝቡ በአንድነት እንደተነሳባቸው ሁሉ ዛሬም ደርግና አድርባዮች በዚህ በያዙት መስመር ከቀጠሉ ወደፊት ከህዝብ ጋር ቅራኔ እንደሚገቡ አንጠራጠርም:: በዓቢታቱ አርሶ አደሩ፣ ወዝአደሩና እንዲሁም ሌሎች ጭቁኖች ከደርግና ከአድርባዮች ጋር የሚያካሂዱት ትግል የዚሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይ ነው:: ስለዚህ የ14ኛው የአብዮት ህብረት ተማሪዎች ዓመታዊ ጉባኤ አገሪቱ ከገባችበት የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የሲቪል ችግሮች ለመውጣት የአገሪቱን አንድነትና ብሔራዊ ነፃነት ወብቶ አብዮቱን ከውጭና ከውስጥ ቀልባሽ ኃይሎች ተከላክሎ ወደፊት ለማራመድ በዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥያቄዎች በአስቸኳይ ሥራ ላይ መዋል አለባቸው ብሎ ያምናል::

ስለ ዲሞክራሲ

የኢት ጭቁን ህዝቦች ከኃይለሥላሴ ፋሽስታዊና የፊውዳል ሥርዓት አገዛዝ ጋር እስከ ዛሬ ድረስ በማያቋርጥ በታላቅ መስዋዕትነት ከታገሉላቸው ጥያቄዎች አንዱ የዲሞክራሲ ጥያቄ ነው:: ዛሬ ይህ ጥያቄ አብዮቱ ከደረሰበት ደረጃና በአጠቃላይ አገሪቱ ከምትገኝበት ሁኔታ የተነሳ አሁኑኑ መፈታት ያለበት አንገብጋቢ ጥያቄ ነው::

የዲሞክራሲ ጥያቄ የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት መሠረታዊ ጥያቄ ነው:: ስለሆነም በየካቲት 66 አብዮት ከፈነዳበት ጀምሮ ሰፊው ህዝብና ተራማጆች ያለማቋረጥ ታግለውታል:: በአንጻሩም የጊ.ወ.አ.ደርግ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ብቻ ባይሆን በሰፊው ህዝብና በተራማጆች ፊት የጭቁኖች የዲሞክራሲ መብት ያለገደብ እንደሚሰጥ በየጊዜው ቃል ገብቷል:: ሆኖም እስከ ዛሬ የጊ.ወ.አ ደርግ የዲሞክራሲ መብቶችን አንቆ በመያዝ አብዮቱን ወደፊት ከማራመድ አግዷል:: ሰፊው ህዝብ የዲሞክራሲ መብቶች ባልተለቀቀለት አንድ ልብ ሊነሳ፣ ሊደራጅና ሊታጠቅ አልቻለም:: ሰፊው ህዝብ በገዛ አብዮቱ ሙሉ ለሙሉ እንዳይሳተፍ በዲሞክራሲ አለመለቀቅ ታፍኖ ተይዟል:: በአንጻሩ በዲሞክራሲ መብቶች ታፍኖ መያዝ የተነሳ አድሃሪዎች እንደልብ የቀልበሳ ሴራቸውን በይ ጋለው ለማካሄድ ችለዋል:: የፀረ-አብዮት ኃይሎች ለመደራጀትና ኃይላቸውን ለማጠናከር ብሎም በአብዮቱና በጭቁን ህዝብ ትግል ጉዳት ለማድረስ ችለዋል:: ስለሆነም:-

— በአሁኑ ጊዜ አብዮቱ ወደፊት እንዲራመድ ወደኋላ የቀረውን የህሊናዊ ሁኔታ በተፈለገው ደረጃ ላይ ለማድረስ ሰፊው ህዝብ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ ስላለበት፣

— ሰፊው ህዝብ በመራራ ትግሉ የተቀዳጃቸው አብዮታዊ ድሎች ከዲሞክራሲ ጥያቄ ጋር በቀጥታ የተያያዙ በመሆናቸው እነዚህን ድሎች በደንብ ሥራ ላይ ለማዋል፣

— የሰፊው ህዝብ አብዮታዊ ድሎችን ለማጨናገፍ ሌት ተቀን ልዩ ልዩ አሻጥሮችን የሚሸርቡትን



አድሃሪ የፊውዳል ቡርዣ ቢሮክራሲ ለመስበርና ህዝባዊ ድሎችን ለማጠናከር

— የወዝአደሩን ፓርቲ፣ ህዝባዊ አብዮታዊ መንግሥትና ህዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊትን ለመፍጠር የሚደረገውን ትግል እንዲፋፋም፣

— የውጭና የውስጥ አድሃሪ ኃይሎች አብዮቱን ለመቀልበስ የሚያካሂዱትን ሴራ በሰፊው ለማጋለጥና ህዝቡም ይህን ሴራ በቀጥታ ተረድቶ እነዚህን ጠላቶች ለማጥፋት በሚደረገው ትግል ሙሉ በሙሉ የነቃ አብዮታዊ ተሳትፎ እንዲያደርግ፣ ሰፊው ህዝብ ከዳር እስከ ዳር እንደ አንድ ሰው ሆኖ እንዲነሳሳና ፀረ-አብዮተኞችን ለመደምሰስ እንዲበቃ፣

— ሰፊው ህዝብ አገሪቱና አብዮቱ በየጊዜው የሚገጥሙትን ችግሮች በግልጽ እንዲወያይበት፣ የመፍጠር ችሎታውም እንዲያበረክት የዲሞክራሲ ጥያቄ ወሳኝ በሆነ ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ እንዲሰጥ::

ለዚህ አቢይ ጥያቄ አለመሟላት በገሃዱ ሊበይነበቂ የሆኑ ምክንያቶች ከየፈርጁ የዲሞክራሲ ጥያቄ እንዳይፈታ የሚታገሉ ኃይሎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አብዮቱ እንዲቀለበስ የሚጥሩና በስልጣን ኮርቻ ላይ ተፈናጠው ለመቅረት የሚሹ ኃይሎች መሆናቸውን ገሀድ ተረጋግጦ ያለአንዳች ርህራሄ ይታገላቸዋል::

ስለ ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ

የጊ.ወ.አ.ደርግ የንዑስ ከበርቴ መንግሥት በመሆኑ ወላዋይነት ያጠቃዋል፣ በውስጡም በያዛቸው ኃይሎች መለዋወጥ ገሪና የማይረጋ መሆኑ ተደጋግሞ ተነግሯል:: ስለሆነም ያቶች ተራማጆች በዚህ በንዑስ ከበርቴ ወላዋይ ጠባይ የተነሳ አብዮታዊ ሂስ የሚለውን በይገባዊ አቋም ይዘው ደርጉን ወደ ህዝብ ወገን ለማምጣት ያልተቋረጠ ትግል አድርገዋል:: አሁንም ያደርጋሉ፣

የደርግ ከህዝብ ጎን መቆም ወይም ያለመቆም የሚወሰነው ደርግ ከአገሪቱ ከሰው ተጨባጭ ሁኔታ ተነስቶ አብዮቱን ወደፊት የሚያራምዱ ወይም ወደኋላ የሚጎትቱ ከሚወስዳቸው እርምጃዎች ነው:: በዚህ መሠረት ደርግ ብዙ አብዮቱን ወደፊት የሚያራምዱ እንዲሁም ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝምን የሚያዳክሙ እርምጃዎች በየጊዜው እንደወሰደና ለዚሁም አብዮታዊ እርምጃ ከተራማጆች ዘንድ ያልተቋረጠ ድጋፍን እንዳገኘ የሚታወቅ ሃቅ ነው:: በአንጻሩም ደርግ አብዮቱን ወደኋላ የሚጎትቱ እርምጃዎችን በወሰደ ቁጥር ሃቀኛ ተራማጆች ዘንድ ሂስም ደርሶበታል:: በአሁኑ ወቅት በተለይ አብዮቱ ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት ከተሸጋገረበት ከመጋቢት 69 ዓ.ም ጀምሮ ያለአንዳች ማቋረጥ እስከ አሁን ድረስ ከያሌ አብዮቱን የሚጎዱ እርምጃዎች በመወሰድ ላይ ይገኛል:: ደርግ በአሁኑ ጊዜ ሃቀኛ ተራማጆችን፣ ታጋይ ወዝአደሮችን፣ አርሶአደሮችን፣ ሴቶችና ወጣቶችን በአጠ

...ው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮትን ፕሮግራም ከሥራ ላይ እንዲውልና የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እንዲሰጥ የሚታገሉ ኃይሎች እንደ ህዝብ ጠላቶች እያሳደደ ያስራል፣ ያሰቃያል፣ ይገድላል፡፡ በሌላ ወገን ከወጣላቸው የህዝብ ጠላቶች በተለይም ከአድኃሪው የፊውዳል ቡርዥ ቢሮክራሲ ጋር በግልጽ ይተባበራል፡፡

ከጭቁን ህዝብና ከሃቀኛ ተራማጆች ይልቅ በውጭ እርዳታና በውጭ ኃይል መመካት ይሻል፡፡ የአብዮቱን ችግሮች ከፖለቲካ ይልቅ በመሣሪያ ኃይል ለመፍታት ይጥራል፡፡ ጭቁን ብሔረሰቦች በማጉላላት ይጨፈጭፋል፡፡ በአስተዳደር ውስጥ ለወጣላቸው አድኃሪ ቢሮክራቶች ሰፊ ቦታዎችን በመስጠት የዘመቻውን አመራር ለዚሁ ለአድኃሪው ቢሮክራሲ በመለቀቅ ዛሬ የአገሪቱን ብሔራዊ ነፃነት ሲደፈር ችሏል፡፡ ስለሆነም ደርግ በአሁኑ ጊዜ ከሃቀኛ ተራማጆችና በሰፊው ህዝብ በፊር በሉን እንዲያስተካክል ጥያቄዎችን፡-

— አብዮቱን ወደፊት ለማራመድና የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በስራ ላይ ለመተርጐም ረገድ እንዲያይታወጅ ታፍኖ የቆየው የጭቁኖችን የዲሞክራሲ መብቶች ያለገደብ አሁኑኑ እንዲለቅ፡-

— በመኢሶን እንዲሁም በሌሎች ሃቀኛ ተራማጆች፣ ታጋይ ወዝአደሮች፣ አርሶአደሮች፣ ሴቶች፣ ወጣቶችና መለዮ ለባሾች ላይ የሚያካሂደውን ጭፍጨፋ፣ ማሰርና ማሰቃየት አሁኑኑ እንዲያቆም፡፡ በየእስር ቤቱ አጉሮ የሚያሰቃያቸውን እነዚህን ተራማጆች በአስቸኳይ እንዲለቅ፡-

— ከጭቁን ህዝብና ከአብዮቱ ዋና ጠላት ከሆነው ከፊውዳል ቡርዥ ቢሮክራሲው ጋር የሚያደርገውን መተባበር አቁሞ፣ ቁልፍ ቦታ የሰጣቸውን አድኃሪ ቢሮክራቶች እንዲያነሳና በእነሱ ሥፍራ ተራማጆችና አገር ወዳዶች እንዲተካ፡-

— ከእርዳታና ከውጭ ኃይል ይልቅ በሰፊው ህዝብ ላይ ተቀዳሚ እምነት እንዲኖረው፡፡ ካለሰፊው ህዝብ ሙሉ ተሳትፎ የፈለገውን ያህል እርዳታ ቢገኝ አብዮት በሰፊው በሰፊው ህዝብ እስከሆነ ድረስ ዘላቂና ወሳኝ ድል ስለማይገኝ፣ ይህን በመገንዘብ ከውጭ የሚገኘውን እርዳታ በአጋዥነት ወስዶ ሰፊው ህዝብ በአብዮቱ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርግ ሃቀኛ ተራማጆች ህዝቡ እንዲነቃ፣ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ የሚያደርጉትን ትግል እንዲፈቅድ፡፡ የህዝቡ ነፃ እርምጃዎች እንደገና እንዲሰጥ፡፡

— በሚደረገው ዘመቻ አመራሩን ከአድኃሪ ቢሮክራሲው ነጥቆ ተራማጆች እንዲይዙት ጥያቄዎችን አቅርቦ ይጠይቃል፣ ለዚህም ይታገላል፡፡



<u>ስለ አድኃሪው ቢሮክራሲ</u>

በየትኛውም ታሪክ እንደታየው ቢሮክራሲ በፍጥረቱ ፀረ-ነፃነት፣ ፀረ-አብዮትና ፀረ-ሰፊ ህዝብ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ቢሮክራሲ አድጎቶ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር፣ እንዲያውም ከቶ ከቶ ያስደገፋቸውን ወሳኙ የሆነው ኢምፔሪያሊዝም ስለሆነ ዘወትር ከሱ ጉያ አይወጣም፡፡ አድኃሪው ቢሮክራሲ ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ተጣግቶ በብዝበዛ ላይ የተመሠረተ ስለሆነ ይህንንም ብዝበዛ ከግቡ ለማድረስ ማንኛውንም አጸያፊ የትግል ዘዴ ማለት ከአሉባልታ እስከ ግድያ ድረስ መሣሪያነት በማመን ዛሬ አገራችን ውስጥ የሚገኘው ቢሮክራሲ፡-

— በማበብ ላይ ያሉት ሕዝባዊ ድርጅቶች የሰፊው ህዝብ የሥልጣን ተነሰቦች ስለሆኑ በቢሮክራሲው ላይ የማያዳግም የበላይነት እንዲያገኙ፣

— በአገራችን ላይ ለሚደርሰው ወረራ ዋና ተጠያቂው ይኸው የፊውዳል ቡርዧዊ ቢሮክራሲው ስለሆነ፣ የአገራችንን ሙሉ ብሔራዊ ነፃነት ከማስደፈሩ በፊት ያለው የሚሊቴሪ ቢሮክራሲ ከአዝማችነት ሥራው እንዲወገድና በተራማጆች እንዲተካ፣

— ቢሮክራሲው ከመንግሥቱ ጋር ተባብሮ ተራማጆችን በማስወገዱ የማሰማራቱን ድርጊቶች እያወገዘ በመቃወም የአሰው የአድኃሪ ቢሮክራሲ የአብዮቱ እድገት እንቅፋት ስለሆነ ያለ ርህራሄ እንዲመታ ጥያቄዎችን ይታገላል፡፡

<u>ስለ ብሔረሰቦች ጥያቄ</u>

ማህበራችን በዚህም በፊት ደግሞ ደጋግሞ በውሳኔዎች አማካኝነት እንደገለፀው ሁሉ ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ከመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለ መብታቸውን ያውቃል፡፡ በተለይ በአሁኑ የኢትዮ ተጨባጭ ሁኔታ የመደብ ትግል ከዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁኑኑ ካለመለቀቅ ጋር እየተሳበ በሚሄድበት ጊዜ የብሔረሰቦች ጥያቄ እየጎላ መምጣቱ ይታያል፡፡ በዚህ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሠረተውን ማርክሲዊ ሌኒናዊ መርህ ተቀብለው ዲሞክራቲክ በሆነ መንገድ ጥያቄአቸው እንዲፈታ ለሚታገሉ ተራማጅ ድርጅቶችና የብሔረሰቦች ንቅናቄ ማህበራችን ሙሉ ድጋፍን ይሰጣል፡፡ በትግልም ከጎናቸው ይሰለፋል፡፡ ይህንን ሀቅ በመሳት በሰበብ በአስባቡ እያወሳገዱ የሚተረጉሙትን የብሔር ትምክህተኞችንና ጠባብ ብሔርተኝነትን ያለማወላወል ይታገላቸዋል፡

<u>ሕዝባዊ ድርጅቶች</u>

አብዮት ያለ ሰፊው ህዝብ ተሳትፎ ግቡን አይመታም፡፡ በአሁኑ ጊዜ በልዩ ልዩ መልክ መቋቋም የጀመሩ ሕዝባዊ ድርጅቶች ወደፊት በሠራተኛው ፓርቲ መሪነት ለሚፈጠረው አብዮታዊ ግንባር መሠረቶች ናቸው፡፡ ስለዚህም እነዚህ ብቅ ብቅ ማለት የጀመሩትን ሕዝባዊ ድርጅቶች ከቢሮክራሲው

ሰዓና በተሳሳተ ሁኔታ ማነሳሳት፣ ማደራጀትና ማስታጠቅ የገነበሩን መሠረት ማጠናከርና የአብ
ሂደት ማሰመር ማለት ነው፡፡ ከዚሁም የተነሳ የመሳው ኢት.ሠ.ማ፣ የሸዋ ክፍለ ሀገር ገ
ዎች ማህበርና የአዲስ አበባ አጠቃላይ የከተማ ነዋሪዎች ማህበር በመሳው ኢት.ሠ.ማ.ሽ.በ
ከጥቅምት 14 እስከ ጥቅምት 17 ቀን 1970 ዓ.ም ባደረጉት ሰበበበ በኢት ጠበቂ ሁ
ላይ ተነጋገረው ያሳለፉት ውሳኔ አብዮታዊ በመሆኑ ጉባኤያችን ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል፣ በሥራ
እንዲተረጎምም ከጎናቸው ቆሞ ይታገላል፡፡ ስለሆነም፡—

— መሪዎቻቸውን ማሠርና መግደል፣ ቅጥቆቻቸውን አያበረቱ አድሃሪዎችን ማስታጠቅ፣ በመጠረ
እነርሱን በቢሮክራሲው ቁጥጥር ሥር ማዋል፣

— የሚያበስሩቸውን አብዮታዊ ውሳኔዎች እየቀለበሱ በሬዲዮ ማሰወሬት፣ በጋዜጣ ማውጣት፣

— ውሳኔው ''የአንድ ድርጅትን አቋም ያንፀባርቃል'' በማለት የህዝቡን አቋሞች መሸር
በጠበቡ መመልከት፣ የጊዜውን አንገብጋቢ ጥያቄዎች አለመረዳት፣

— ሳሳለፈው ውሳኔ ልክ አለመሆን በቂ ምክንያት ባይበው ተጨፈሪ ውሳኔ ''ከምንተር ፊዘ
ን''ክሥር ሠራተኛው እንደገና እንዲያበልፍ ማበፈፈሪትና መቀስቀስ፣ሠራተኛውን እርስ
በራሱ ለማጋጨት የሚደረጉ ሙከራዎች ስለሆኑ እነኚህን ፀረ-አብዮትና ፀረ-ህዝባዊ ድር
ቶች ተግባራት የሚያስኬዱትን ደርግንና ከአቋማቸው የተንሸራተቱ ''ተራማጅ'' ድርጅ
ጉባኤው በጥብቅ ያወግዛል፡፡

እንዲሁም ደግሞ ተራማጅ ውሳኔዎች በአንዳንድ አከባቢ ቢያልፉ ለአንዛያ ህዝባዊ ድርጅቶች
እየደወሉ ''የፈረሰውን ኢሰአማን ሆናችሁ አይደለም?'' እያሉ ማበፈፈሪት እንደ ኢሰአማ
ፈርሰናችሁ አለን ወደሚለው አቋም በለሚበበ ደርግና መበሉቶች ከዚህ አይነት የሚፈረፈርጠ ዛቻ
ሊቆጠቡ እንጠይቃለን፡፡

ኢ.ሴ.አ.ን

ሴቶች በቀጥር የህብረተሰቡ ክፍሉ ትግል ገማች ናቸው፡፡ ግን በሴትነታቸው ብቻ በፊውዳሉ
ስርዓተ ማህበር የተደረረቡ ጭቆናዎች እንደደረሰባቸው ዛሬም እንዳልተሳቀቀ ግልጽ ነው፡፡
በዚሁም የተነሳ ለአብዮቱ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ በመጠነ አነስተኛ ነው፡፡ ስለዚህም
ማህበራችን ''ሴቶች ይደራጁ፣ለአብዮቱ እንዲበቁ''በሚል መፈክር ስር ቢታገል ቆይቷል፡፡
ይህንንም በተግባር ለመተርጎም በሚያዝያ 1969 ዓ ም የወጣውን (የኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ
ንቅናቄ, ኢሴአን) ፕሮግራም ተራማጅነትና በልሳንነቱ ''ታጋይ ኢትዮጵያዊት''አማካይነት በገ
ዚያዊ አንገብጋቢ ጥያቄ የምትበጫቸውን ትንተናዎች ትክክለኛነት በመገንዘብ ማህበራችን ለዚህ
ንቅናቄ ያልተቆጠበ ድጋፉን ይሰጣል፡፡ አሁን በቀርብ ጊዜ ወጣዉ በንቅናቄው መሪነት



በጨረጨራቸውና በሌሎች ታጋይ ወጣት ሴቶች ላይ የሚደረገውን ዘመቻ ኢህዝባዊ ማስታዩት ጉባ
ኤያችን ያወግዛል፡፡

ያሉ ህዝባዊ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ተብትና አብዮቱ ሊካሄዱ ስለማይችል፡—

— ህዝባዊ ድርጅቶች በአብዮቱ አገባር እንዲቆሙ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ
አሁኑኑ እንዲለቀቁ፣

— የታሰሩ መሪዎቻቸውና አባሎቻቸው በአስቸኳይ እንዲፈቱ፣ ድርጊቱ በአስቸኳይ እንዲቆም፣

— በሬውን ህዝብ በማስተማርና በማደራጀት ላይ ባሉ ከህዝባዊ ድርጅቶች ጋር እየተለቀሙ
የታሰሩት ገቂኛ ተራማጆች በአስቸኳይ ተፈተው በቀያዩቸው መሠረት ለህዝባዊ ድርጅቶች
እንዲመለሱላቸው፣

— ያሉትና ወደፊትም የሚፈጠሩት ህዝባዊ ድርጅቶች ከቢሮክራሲው ተጽእኖ ነፃ በሆነ መንገድ
እንዲደራጁ፣

— አድሃሪዎችን የሚጋለጥና ነፃ እርምጃ የሚወስድ መብታቸው ታውቆ በድርጊት እንዲተረጎም
ጉባኤው ይጠይቃል፡፡

ስለ ኢ.አ.ወ.ን

ኢአወን (ኢት አብዮታዊ የወጣቶች ንቅናቄ) በመባል የታወቀው የወጣት ንቅናቄ በመሰከረም ወር
ሚስጥራዊ መቀቀሩን ባይገልጽ መርሀ ግብሩን በይፋ አስታውቋል፡፡ ይህ የወጣት ንቅናቄ ትናንት
በኢህአፓ ቁጥጥር ስር የነበረውን ወጣት ዛሬ ወደአብዮቱ ሠፈር ለመቀሳቀል የቻለው ጠከናተኛ
የርእዮት አለም ትግል እንደሆነ ማህበራችን ያምናል፡፡ ይህ የወጣት ንቅናቄ ትናንትና በሀገራ
ችን ወጣት ሁሉ በጅምላ እንደአብዮታዊ የሚቆጠርበትን (myth) እምነት በበር ከወጣትም መሃል
የመደብ ትግል እንዳለ፣ወጣት በአጠቃላይ ተራማጅ እንዳልሆነ በገሃዱ አሳይቷል፡፡ በተለይም
ለረጅም ጊዜ ማህበራችን የሚከተል የነበረውን አብዮታዊ መርሀ ''ተማሪዎና ምሁር ከገበሬውና
ከሰራተኛው ጋር ተዋህደው፣ከነሱም ተማር፣መልሰህም አስተምር''በመከተሉ ጉባኤው አድናቆቱን
ይሰጠዋል፡፡ በተጨማሪም የወጣት ንቅናቄው የመኢሶን ወጣት ክንፍ እንደሆነ ከፕሮግራሙ እን
ረዳለን፡፡ መኢሶን በኢት አብዮት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የተጫወተ አንጋፋ ማርክሲስት ሌኒኒስት
ድርጅት በመሆኑና ኢአወንም የእሱ ክንፍ በመሆኑ ከእሱ ምንጩ ነጥሎን መመልከት ስለማይቻል፡፡

— በልሳኑ በአብዮት ፋና አማካኝነት ሰበበት ዓመታት ያህል ያስተጋባቸውን ቀስቀሳዎችና
ፕሮፓጋንዳዎች በመመልከት፣

...ዲቶችን በአብዮቱ ሠፈር ለመሰብሰብ ያደረገውን ያልታከተ ጥረትና ያገኘውን ውጤት በመረ ዳት፣

— ታሪካዊው ፍሎሙ ማህበራችን ከሚታገልለት የፖለቲካ መስመር ጋር አንድና ትክክለኛ በመሆኑ ይህ ዝግጅ ለወጪት ነቀና ጭ ያለ ድጋፉን ይበዛል:: ከጎኑም ተሰልፍ ይታገላል::

ስለ ተራማጅ ድርጅቶችና ተጃመር ስለነበረው ሁኔታ

ማህበራችን ከብዙ ዘመን ጀምሮ በሀገራችን ውስጥ ተራማጅ የሆኑ ድርጅቶች አንዲያበቡ ያልተቋረጠ ጥረት አድርጓል:: የተራማጅ ድርጅቶች መኖራቸውና ማበብ የአብዮቱ የበላይ አንደሆነ ዛሬም ማህበራችን ያለመዘረዘር ያምንበታል:: በዚህም ጥያቄ ላይ የሰጠየቱ ጽኑ ገፍና ማህበርም ሆነ የኢሕማ ያለማቋረጥ ትልቅ ጥበብ አድርገዋል::

ባለፈት ጥቂት ወረት በአገራችን ውስጥ አምስቱ ማሌዶች ሁኔታ ፈጥረው አብዮቱን ለማገልገል ተነስተዋል ባለበት ጊዜ ማህበራችን ከሌሎች እህት ቀ|ማህበራት ጋር በአንድ ጎጆ ለዚሁ ተራማ ር ለነበረው ሁኔታ ድጋፍን በቀጥታ እንደነበር ይታወቃል:: ይህ ድጋፍ ፍሎሙ ትክክልና ከአ ለንዶ የአብዮቱ ወዳጅነት አንፃር ቢታይ ድርጅታችን ላብዙ ጊዜ ቢታገል የቆየና ወደፊትም የሚ ታገልለት በለሆነ በተወሰደውም አቋም ሆነ ወደፊትም የሚሊዶ ሁኔታ በሚመለከተው በኩል ያለንና የሚኖረን አቋም እውነተኛ የማሌዶች ሁኔታ ብቻ ነው:: ለአምስቱ ድርጅቶች ድጋፋችንን በሰ ጠንበት ወቅት የተመለከትናቸው ዋና ዋና ነቀቦች:-

— ድርጅቶቹ በለወዝአደር ፓርቲ አፈጣጠር ያላቸውን አንድ አይነት በመሆን በመመልከት፣
— ድርጅቶቹ በአድሃሪው ቢሮክራሲው ላይ ስለነበራቸው አቋም፣
— ድርጅቶቹ በብሔረሰብ ጥያቄ ላይ ስለነበራቸው አቋም፣
— የየገሉ ፕሮግራማቸው በመመርመርና
— በአጠቃላይ አብዮታዊ ፕሮግራም ተግባሩ በስራ ላይ ከመዋል አንፃር በማየት ነበር::

ዛሬ ግን ከእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ኢጭአትና መኢሶን በአቋማቸው ፀንተው ቢገኙ የተቀሩት ሰበት ድርጅቶች የአብዮ ፕሮግራም በመብራ ላይ በመሆናቸው የፈለቸውን መርሀ ገብርና በጋራ የዐቁወንም በመሆኑ ግምር በመዲበቸው ይህ ዝግጅ ለሶስቱ ድርጅቶች (ሰደድ፣ ማሌሪድና የወዝ አደር ሊግ) በህብረቱ በጋራ በቀጥታ የነበረውን ድጋፍ አያነሳ በተለይ በአንድም ወገን የአብዮቱን ሠፈር ለማ ያዳክመው ለመኢሶን ዝግጅቱ የማያወላውል ድጋፍን እየሰጠ ለተፈጥሮ በዚህ ሁኔታ ለሚታገሉ እንደ ኢጭአት ላሉ ድርጅቶች ድጋፍን በማደስ ሌሎች ቀን ተራማጆች፣ አገር ወዳድ ድርጅቶችና ግለሰቦች በተቻለ መጠን ከእነዚህ አድርባይ ድርጅቶች በመለየት ወደአብዮቱ ሠፈር እንዲሰበሰቡ



ጥረትን ያደርጋል:: እንደ "ኦፕ–ፊና" ያሉትን ለፍርፋሬ ያደፈጡን ዝግጅቶች በቅጥቀ ይቀ ጋሳል:: አድርባይ ድርጅቶች ለፈተና ጊዜ ያለ የሚሉትን የብሔር በረሃ አስነት ፓርቲ አያገባቸውን ገንዘ ተራማጆች በሙሉ ነቅተው እንዲጠብቁ ዝግጅቶችን ጥረትን ያደርጋል::

ስለ ተራማጆች መታሰርና መገደል

የጊ.ወ.አ.ደርግና አብዮታዊ በርክሔበ ዛሬ ቀን ተቀን ተራማጆች ለሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች የሚ ሆን ጆሮ በመስጠት በተለይ መኢሶን ለሚያነሳቸው አቢዮታዊ ጥያቄዎች ከመኢሶን በመበገዘ ፊቶው ብቻ ፈታኝ በአመሆናቸውና እንዲያውም በተቃራኒ ከጎን መንገድ ወዶ የነበሩትና የታ ወቀን አባላት ገደል ለመበረሰ የተደረገውን ወቀን መኢሶን ለአደረሰበት (ለወ ሀዘን ሰመ.ቶ ዕት መሐሪት) በዚህ ሁኔታ በኋላም ለአብዮቱ የበለጠ ከስተቶች ጥፋትን የሚያስከትል ጉዳይ መንገድ መቃወም የተነሳ፡ በዚህ መሆኑ ከወ ቶገሳ ወዘዉ መታወቅ በዘበራ አስቸሮታል:: ይህን በማድረጉ አብዮታዊ በርክሔበ ጊ.ወ.አ.ደርግ በዚህ ድርጅት ላይ የወሰደውን የጭቆና እርምጃ ሌሎችም ተራማጆችን በቀጥታ አስጠንቅቋል:: ለምሳሌም:-

— መኢሶን አወነተኛ ማርክሲስት ሌኒኒስት ሊያደርግ የሚገባውን የትግል ዘዴ በመጠቀሙ ህጋዊ ሆ፣ ወደ፣ ጫጣሪ ነጻነቱ፣ በሰላም ለመ...፦

— መኢሶን በአጭር ጊዜ የኢት ዮጵያ ውስጥ የቋንቋና ዥረት ብሔረ ለማጥናት በመጀመሩ ሀ ሉ ትምህርት ለፈ ማጥበት ያለባቸው ማህበሩ ይዘጋጃሉ::

ነኝ፡-
— ይህንን የትግል ዘዴ የሚያውቀው ፋሽስቶች፣ መኢሶን ከበርክሔበው ጋራና ከፍርፋሬ ህዝብን መርዶ ወደ ህዝብ ለማገዝ "ፈርጨ" የሚሉትን በቀጥታ ያወግዛል::

— ከአቋማቸው ተነሽፊታቸው፡ የአብዮት ፕሮግራምን ከአቶው፣ የሚመከሉበት አስፈላጊነት ከወዉ ወደ ቶኝ የሚረገውን ለአካሉ የሚገባቸውን "ተንሽፊታች" የሚሉት መኢሶን ድርጅቱ በፍፁም ከሥሬው ጋር ያልተያዘ በመሆኑ ዝግጅቱ ይህንን አወፈር ቀጽና መሆኑን ተገንዝቦ ለድርጅቱ የዘመን አይነት መዉፈኝ የሰውን ያወግዛል:: ይታገላቸዋል::

በመቀሬም፡-

— መኢሶን የወቀኝው ጥያቄዎች ከሥራ ላይ እንዲውሉ እየታገለን በድርጅቱ አባላት ላይ የሚደረገው መታሰርና መገደል በአስቸኳይ እንዲቆም፣

— የታሰሩት ጓዶቻ ተራማጆች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይህ ዝግጅት ይጠይቃል:: በጓዶቻ ተራማጆች ላይ ለሚደርሰው ጉዳ ለማን ሀላፊ ነው ?

## ሠራዊትን በሚመለከት

የኢትዮጵያ ሠራዊት የሰፊው ህዝብ አካል ነው፡፡ የተሟላ ስልጠና ከዘመናዊ መሣሪያ ጋር ከሆነ እንደሆነ ኃይሉ የሚጠበቅ ነገ ነው፡፡ ወልቆ ለጠላት ያለው ድርሻ በዝብዞታል፤ ከውጭ የ ታሪኩ፡፡ ይህንንም ድርሻ ፕሮፓ ለመቋቋም ከሰፊው ጭቁን ጋር በፈቃድ በመሰለፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ እያደረገም ነው፡፡ በፈቃድ በጠነከረ ትግል እዚህ የደረሰው አብዮ ታችን እንዲጠናከር ነቀፋ የመጠበቅ አብዮታዊ ግዴታ ተሰፊነት እንዲሰበት፣ እንደሚጠበቀው ሚሊሻችን አይደረስበትም፡፡ ስለዚህ፡-

በዚህም

- የኢትዮ ፕሮግራም ከሥራ ላይ ጥቁር ሠራዊት ጭምር ያፈሰሰበት አብዮት እንዲጠናከር የሚያደርገውን ትግል በጽናት እንዲያፋፍም፤

- የአብዮቱ አስተማማኝ ነጻነት ዲሞክራሲያዊ ኃይሉ መሆኑን የሚያውቀው ሰፊው ሠራዊት ይህንን በፈጸሙ ሁኔታ ሊያሰፋ የሚችለው የመከራከሪያ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እንዲኖር እና የአብዮቱ የሚያደርገውም ትግል ከሰፊው ህዝብ ጋር እንዲያፋፍም፤

- የአብዮቱ ጠላት የሆነው የሶሻል ሆነ የሚሊተሪ ቢሮክራሲውን የሚያጋልጥ ትግል መግለጽ እንዲያካሂድ፤

- በቢሮክራሲው ሹመር የያዙት ገዢ ቡድኖችን ለማስለያየት በቀን ዲሞክራሲ ላይ የሚወጡ ሕጎች ዐይነ እርዳታ ለማግኘት የሚፈልጉትን ትግል ከኢት ጭቁኖች ጋር አስተባብሮ በጽናት እንዲያካሂድ፤ እኛም ጠላትነቱ ትግሉን ከንቱ የሆነ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እየገለጽን ሠራዊቱ ተገቢ እንዲታገልበትና እንዲያታግልበት አብዮታዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡

## የሚሊሻ በመቋቋም ያካሄደው ወረራ

የሚሊሻ የገዥ መደብ የመከፋፈት አላማን ከገበ ለማስፈጸም ሰሜን በዙ ክፍሎች ዘገየች ደሀ ደርግ ከርዩ በሰሜኑም ከበ ተጨፍና በአከባቢው ገበር መሣሪያ በመጠኑና በአጠቃላይ አሁን ከዚህ በፊት ተነሳስቶ በአብዮታዊነት ድንበር ቀበ በመገበት ጭቁኖችን አምራቾች ግዛታዊ ሀገን አንድነቱ ጉዳል አየቸለ፡፡ አውቆው የሚሊሻ የገዥ መደብ ለበቀረበቸ ነገርና አሜሪካዊ የሚያካሄደው ወረራ አንደገና ፀረ-ኢትዮጵያና የሚሊሻ ጭቁን ህዝቦች በመሆኑ በጣም እያወገዝን፤ እንታገለዋለን፤ ተራማጅ ኃይሎች ሁሉ እንዲታገሉት ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡ ከዚህም ከሚሊሻ ወረራ ለመዳን የተባለው ''ህዝባዊ ድር''በሚሊተሪ ቢሮክራሲው አገዛዝነት ሥር በመቋቋም በመተባበር አብዮታዊ ከመሬ ቢሊየንና በዙ የነት እንደደረሰበት ገባው ተደርጎ ''ህዝባዊ ፀሩ''አብዮታዊ ከመሬ እንዳንገኝ ይመስላል ያስገዳል፡፡ ለአብዮታዊ ስሜ ቱ ማህበሩ አዋቂ ይያገሻል፡፡



## የአገሬና ገቡ መቃብር ነው፡

አዎ ጓዶች ይሁን በራቸ ይሁን ከሳሽ ዎገደና
የአርማ ሌባ አበሳ ባይ አገደና
መስሎት ሰቶ ማጠም እውነትን መጨፍለቅ የሚቻል
ተነሳ ዲሞክራሲን በመበበ ሊያስመስል ግን
ዲሞክራሲ ገርሻ አይደለም ለጭቁኖች ተመችና የሚሰጥ
መብት አገኙ አገደናን አደር ባይ አናርኪስትን ቢሮክራትን የሚያራውጥ
አሉባልታን የሚያጠፋ
ቀልባሽን የሚያጋልጥ የሚደፋ
ዲሞክራሲ መካሪያ ነው የጭቁን ደሃና ተስፋ
አዎ ጓዶች ይሁን በራቸ ይሁን ከሳሽ ዎገደና
የአርማ ሌባ አበሳ ባይ አገደና
''ዲሞክራሲ በትግል'' ይበለን
የደገፉት ትግል ሊያስተምረን
.ገራ መስሎ ሊጭኝን
በትግል መሆኑን ወቶ አጣሁት ያውም የከረረ ትግል
ገን ተጨባጭ መፈከር መያዝ ያስፈልጋል ለመታገል ለማታገል
ብሎ ብሎ '' ቀላሁ''ይበል ያ አደር ባይ ያ ወላዋይ
በቀኝም አስመሳይ
በታጋዮች ደም ሲነገድ
የትግሉን ወሳፊን ሲያበርዱ — ጭቆኑ የዲሞክራሲን መብት ሲገድሉ
አዎ ጓዶች ይሁን ብራቸ ይሁን ከሳሽ ዎገደና
የአርማ ሌባ አበሳ ባይ አገደና
የጭቁኖችን ዲሞክራሲ ሊያፍን ሊያሰፍን
'' ቀይ ፋና '' ይዞ ቀዮችን ሰወጋ አያየን
የገራ መስመር ታጋይ ነኝ ይበለን? ሊጭኝን
ቀለባሽ አደር ባይ አገደና
ከቶ ፍጹም አዝነ አይሆንም ለና
አይቶን የለም የትርክቢን አገዳ የሚገከሽክ ኞን

የአኳኋን አሰከሩ የቀሰበሸችን
እዚያስ በሩቢያ አገኙ ወቸ ተሳካ ፀደመ አገኚ ተገከ ቃከቶ
ቀመታ አገኚተደመሰሰ ከርስ መያበር ተከተተ
አየት ጓደች ይሁን በራቸ ይሁን ከላሸ ምንደኛ
የአርማ ሌባ እበላ ባይ አንደኛ
የሁለት መበመር ትግል ነው ይበል?
አዶር ባይ ነቱ ሲያይል
ሰባሰበት
ሲያያዘው ምኞት
ጊዜው የደረሰ መስሎት ልቅን ሊያገቅ ባይንስን ለቦርዝ
ሎቆቹን ሊያስጨፈጭፍ ሊያስፀግዝ
ፀዝለደረን ሊያፀናብዉ ታጋዮችን ለክፋፍለ
ዒዒቱውን ነስነሰ ውሸቱን እውነት ሊያስመስል
አየት ጓደች ይሁን በራቸ ይሁን ከላሸ ምንደኛ
የአርማ ሌባ እበላ ባይ አንደኛ
ለሰበማዎ ይበል የሰፊውን ህዝብ ድምጽ
ሲያስተጋባ ጎቶከራሲ ለጭቆኞች ያለገደብ እያለ በገለጸ
ድምጽ ሲሰማ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ - ከጫለታ እስከ ጫለታ
ጭጭ አርጭ ሊያደርገ የአዉሃሬን ዉጅንበር ወኪታ አሰባሰታ
ንግሬት ጓደች ለዚህ ደንቆሮ አንደኛ
የተራማጅ ትግል እንደማይ ታጠፍ የሰቆኛ
ንገሬት የተራማጅነት ተርጉም ምን እንደሆነ- የሰብዮት የነጻነት
እንደማንሽ ባርነት የቢሮከራሲ ተምሳሌነት
መሣሪያችን እንደሆነ የጎቶከራሲ መበት
አንገብጋቢነቱ ሰበላዎ ሰጠር ነትዎ ለአብዮት
ንገሬት ይታረዎ እንደሆነ ይታረዎ
ማሸመሬን ማሸከከሸኩን ያዎ
አየት ጓደች ይሁን በራሽ ከላሸ ምንደኛ



የአርማ ሌባ እበላ ባይ አንደኛ
ፀሸገዝር ነሸ አገኝ ፈጪፊ
ሲዩገብ በራ መስሎት ኳለታ መዉሬ
ማርክሲዝም ቁት መቀበር መስሎት የፀምጽ በለጪ
ፀይ ፍንከች ፀይ ንቅንቅ ምዉሬ አደር ባይ በንጪ
የፀሬ መስመራችንን ይዘን ማርክሲዝምን እያነበርን እያጠፋን
እስከ መፀረሻው ገበ እንገዝፋን ከጭቆኞች ተያቅረን
አየት ጓደች ይሁን በራሽ ይሁን ከላሸ ምንደኛ
የአርማ ሌባ እበላ ባይ አንደኛ
ይህ በው እከ ጆሮ አለገበዎ
ሒጽን አለተረዳዎ
ባይንሶን እነበበ እንዲ አለኝከዎ አለቀፀዎ
ኳያለከ ቋከዎ አለተቋዩዎ
የሰቆኞችን ህበዐ መግቢት
ከሰፊው ህዝብ ጋር ልብ ለልብ መገናኘት
በሉ ይጥሬ " እባፋሬ ሸስት "
ዓሥን በፃል ከቢሮክራሲው ለመጋቢት
አለገዝዎ እከ ምኝ እንደሆነ ህበዐ ማለት
የፀዝለደሬ የአርስ አደሬ የወያደሬ የበሻሌት
አንዱነትና ንበረት
ለላነበበ እከ ምሁራን ምርጥ ሥራ ጀች
አመፈርን ከሰፊው [illegible] ዓዋዩ ዘዳያችና መሬህያች
አየት ጓደች ይሁን በራሽ ይሁን ከላሸ ምንደኛ
የአርማ ሌባ እበላ ባይ አንደኛ
ቀለከሾ ዓይን በዓይን ሲያዩና
የራስ መተማመንን ተርጉም ሲያዩና

እያወቀ የጨቋኞችን የጩራ አቋም
እንደሊሳው ሁሉ በራስ የመተማመን ጥያቄ
አሁንም ይገባው ጥገኝነት እንደማይጠቅም
ይረዳ አስፈላጊነትን በራስ እግሮች የመቆም
እቶት ጓዶች ይሁን በራዥ ይሁን ከላሽ ምንደኛ
የአርማ ሌባ አንጃና
ወሬኛ አለኝ ይበል?
ጨቋኞችን ለመነጃል
የአለባሰታ ወሬኛ ሰብሳቢ
የምንቅ በስና ተገብጋቢ
ጨቋኞችን ወከሉ ሊገባ ከጓደኞ ሊቀላቀል
ሊሄድ ከሳይገሩ ርቆ ከመሰሉቹ ሊጓበል
በሁለት መስመር ትግል በናምገም
ከተራ ምንደኛ ጋር አይደለም
ይሁን ብንልም አይሆንም _ ምክንያቱም
የአርሱ ቀጥረኝነት እንጂ የመስመር ትግል አይደለም
ምክንያቱም _ የመስመር ታጋይ ጨቋኝን አያበገድልም
ይከራከራል እንጂ ሸገጡን ገተር
የርዕዮተ ዓለም ትግል ያቀጣጥላል እንጂ አምርር
እንጋፋ ወሬኞችን አያባብርም
ከቢሮክራሰው አይጋባም _ አያሻጥርም
አብዮታዊ ገበረገብነትን አይከዳም
እቶት ጓዶች ይሁን በራዥ ይሁን ከላሽ ምንደኛ
የአርማ ሌባ እበላ ባይ አነጃና
የጨቋኞች መስመር አሸናፊ ነው
የአንጃና ገቡ መቃብር ነው

ከንጋቱ ብርሃን

## ማ=ሳ=ሰ=ቢ=ያ

ውድ አንባቢያቻችን፣

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አሁን በደረሰበት ደረጃ በአ.ኢ.ተማ የሰፊውን ሕዝብ ትግል በበለጠ ማስተጋባትና በበለጠ ከሰፊው ሕዝብ ጎን መቆም አለበት:: እስከዛሬም ድረስ መጽሔቶቻችን፤ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል በማስተጋባት፣ በማስተማርና በመቀስቀስ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ እሙን ነው::

ባሁኑ ወቀት በምዕራብ አውሮፖ አገሮች ባለው የኢኮኖሚ ቀውስ የተነሳ የፖስታቤት፣ የወረቀቶች፣ በጠቅላላው የዕቃዎች ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ መጥቶዋል:: ይህም በአ.ኢ.ተማ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴና በመጽሔት ቦርድ ላይ ከፍ ያለ ወጭ አስከትሏል:: የገንዘብ ችግር ለሥራችን ፍጹም እደናቃፊ ሆኗል::

ውድ አንባቢያቻችን፤ የአ.ኢ.ተማን ሥራ አስኪያጅና መጽሔት ቦርዱን በተቻለ መጠን ችግሮቻቸውን እንዲወጡትና የኢትዮጵያንም ሕዝብ አብዮታዊ ትግል ይበልጥ እንዲያስተጋቡ፣ የማስተማርና የመቀስቀሻ ሚናቸውን ይበልጥ እንዲቀጥሉ፣ የገንዘብ ችግራችንን ለማቃለል ትረዱን ዘንድ አብዮታዊ ጥሪያችንን እናቀርብላችኋለን::

ዕርዳታ ማድረግ የምትፈቅዱ ሁሉ በአ.ኢ.ተማ በገንዘብ ያዥ በኩል በተለመደው አድራሻችን /P.O.Box 3198 103 64 STOCKHOLM 3 SWEDEN / ልትልኩልን ትችላላችሁ::

በአብዮታዊ ምስጋና ጋር

በአ.ኢ.ተማ መጽሔት ቦርድ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፤

የጠውን ገትና ቱ ከውስጥ ሆኖ ቦርቦር ለማድከም ያደረገው ሙከራ ስላልተሳካለት እርሱን ከገቶናቱያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከተርበ ጊዜ ጀምሮ፤ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጉን በመሰለፍ ያለማቋረጥ ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግሉ ሲያካሄድ በኖረው ማህበራችንና በነዚህም አስር ዓመታት ያስተሰጣቸውን ነፃ'ት በመገጠቀ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግለ ሲያስተጋቡ በኖረት ፓከ የተናጠው የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መተስተሻ ሆነው በቆዩት በ<u>ታጠቅና</u> በ<u>ትግላችን</u> ስም መጠቀም ጀምረዋል፡፡ የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም <u>ታጠቅና</u> <u>ትግላችን</u> በአስር ዓመት ቆራጥ ትግለ ባተረፈት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው፡፡እንዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያታለውን የኢትዮጵያ ተማሪያችና ተራማጆች አንድነት የማፍለስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ወንጀበር በመገዛት ለማፋፋም ነው፡፡ይህም እንደማይሳካ የተረጋገጠ ነው፡፡ ለማገናዘብ፤የተለመደው መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለያዙ፤የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች <u>ማህበር</u> አባልነትን የማያመለከት ገን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንዲታወቁልንና እንድታስታውቁልን እንጠይቃለን፡፡ለእነዚሁ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው ''ባለም ዓቀፍ ሪፓርቶን'' በሚባል ስም የታወቀው የነ አሰፋወሰን — መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት ነው፡፡

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በኢሴተማ መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ